# BACKGROUND

The Institute for Peace and Security Studies (IPSS) of Addis Ababa University and the Peace Research Facility (PRF) of the Rift Valley Institute (RVI) jointly organized a seminar on the theme 'Rethinking Ethiopia: A Seminar on Youth Voices', held on 22 February 2024. The seminar was based on a call for submissions that these organizations made in September 2023, requesting essays commemorating the 50th anniversary of the 1974 Ethiopian revolution.

The Ethiopian revolution marks a significant turning point in Ethiopian history, bringing about major social and political changes with far-reaching consequences. In commemorating the 50th anniversary of this historic moment, it is important to reflect on this legacy and the lessons that can be drawn from it. Moreover, the ideas discussed and debated at that time remain central to public life in contemporary Ethiopia. The Institute for Peace and Security Studies (IPSS) of Addis Ababa University and the Peace Research Facility (PRF) of the Rift Valley Institute (RVI) provided a national platform for further articulation, exchange and debate about the future(s) of Ethiopia.

To this end, these organizations invited young Ethiopians (18 to 35 years old) to contribute their ideas, in the form of a 2000-word essay, on what they take to be the contemporary challenges in Ethiopia and to propose solutions from variety of disciplinary backgrounds. The essay competition was intended as an opportunity for young writers to assess the legacy of the Ethiopian student movement and revolution, identify the main causes of current predicament(s) facing the country and look ahead to the next 50 years. Through this initiative, the host institutes aimed to provide a national platform for young Ethiopians to discuss and debate the challenges and contradictions facing the country and to propose solutions to make Ethiopia a more peaceful and prosperous nation for all its citizens.

Those wishing to submit an essay were instructed to outline an analysis of their view of the Ethiopian problem(s) and proposed solution(s). Contributions were welcomed from all disciplines and backgrounds and were not expected to be heavily referenced. The call for ideas was advertised on 12 September 2023 (https://ipss-addis.org/call-for-submissions-rethinking-ethiopia-a-call-for-youth-voices/), which coincides with the date that *Atse* (King of Kings) Haile Selassie I was deposed from office. Given internet shutdowns affecting some parts of the country, particularly Amhara region, we sought to ensure equitable representation and participation from across the country. To this end, we assigned focal persons as the primary point of contact in Gondar, Bahir Dar, Dessie and Debre Birhan.

We received more than 40 submissions in four different languages: English, Amharic, Afaan Oromo and Somali. These submissions came from several areas, including Addis Ababa, Oromia, Amhara, Somali, Southwest region and Central region. A panel composed of 4 RVI and IPSS representatives reviewed the submissions based on agreed selection criteria that focused on originality, progressive value and clarity of thought of the proposed recommendations. Ensuring a diversity of voices (societal, sex) was also a key consideration.

The panel then selected 15 contributors, who received mentorship to further refine and shape their essays. The 15 selected semi-finalists received writing mentorship from esteemed Ethiopian scholars: Dr Serawit Debele, Dr Netsanet Gebremichael, Dr Kiya Gezahegn, Dr Mercy Fekadu, Dr Yonas Ashine and Shimellis Hailu. These mentors were selected for their expertise, diverse educational background and capacity, and willingness to work with and mentor the young contributors. After a month-long mentorship process, the mentees submitted their final essays.

The final version of these 15 submissions were reviewed by a four-member group from the RVI and the IPSS to select the 5 best essays for presentation to a wider audience at the seminar in February 2024 and for publication in a range of languages: Amharic, Afaan Oromo, Tigrigna, Somali and English. The same agreed criteria were used to select the essay finalists: originality, progressive value and clarity of thought. We also aimed for gender-balanced group of finalists, with two young women and three young men selected. Among the five finalists, two are undergraduate students in their final year, one is a MA candidate, one is a graduate degree holder, and one is a recent LL. B graduate. Three are based in Addis Ababa, one is from Debre Birhan in Amhara region, and one is from Hawassa in Sidama region.

The seminar on 22 February 2024 was organized with the intention of providing the selected essay finalists an opportunity to present their work to a wider audience. It also intended to solicit reflections on the last 50 years since the 1974 revolution from scholars familiar with relevant social, economic and political issues. The seminar report is published and can be accessed at organising institutions websites [https://ipss-addis.org/; https://riftvalley.net/]. This bulletin contains the Amharic version of the essays. We are hopeful it would make the essays accessible to a wider audience. We would like to express our gratitude for the essayists and translators and everyone else who made this possible.

## ቤተልሔም ሞላ: ሀገር እና ሃሳብ: ምሁራኖቻችን ድሮ እና ዘንድሮ

“ሀገር ማለት ሠው ማለት ነው!” ስንል ሀገር ማለት በሠዎች ውስጥ የነገሠች ሀሳብ ናት ማለት ነው ብየ አምናለሁ። ሠወች ሀሳባቸውን እንደሚኖሩ በተለያየ አጋጣሚ በመንፈሳዊዉም፣ በማህበራዊውም አውድ ሲነገር እንሠማለን። ሃገር ደግሞ በትክክል ሰዎች በምናባቸው ፈጥረዋት ሃሳባቸውን ሙሉ ለሙሉ የምትቆጣጠር ድንቅ ሃሳብ ናት። ሃገራችን ኢትዮጲያ ለብዙ ሺ አመታት በተለያዩ ትውልዶች በተለያየ ሃሳብ ህዝቡን አንድ አድርጎ በሚያቆይ መንገድ እየተገነባች ከትውልድ ትውልድ የተላለፈች ሃገር ናት። በተለይ ግን የዚህ ጽሁፍ ትኩረት የሆነውን ከ1960ዎቹ ጀምሮ ሃገራችን እየተገነባችበት የመጣችበትን የሙህራን ሃሳብ ፍሰት ስንመለከተው፤ መገፋትና ማወቅ የወለዳቸው ጥያቄዎች ህዝብ አነቃንቀው ለብዙ ሺ አመታት ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር የቆየው የዘውዳዊ ስርዐት ሊወድቅ ችሏል። በመሆኑም ሶሻሊስት ኢትዮጲያ ተመስርታ የመሬት ለገበሬው ጥያቄ መልስ አግኝቶ ጭሰኛው የመሬት ባለቤትም ሆኗል:: ነገር ግን ቅዠት በሚመስል መልኩ የአብዮቱ ሃሳብ አመንጭዎች ሳይቀር አብዮት “ልጆቿን ትበላለች” በሚል ብሂል የጥይት ሲሳይ መሆናቸው፣ ነጻ የሃሳብ ፍሰት መከልከሉ፣ ስርዐቱ አሃዳዊ እና ወታደራዊ መሆኑ፣ ወጣት በሃገሩ ከማበብ ይልቅ መሞቱ፣ መቁሰሉ እና መሰደዱ ለሌላ ጭቆና የወለደው የትግል ሃሳብ መፈጠር ምክንያት ሆኗል። በዚህም ምክንያት ለ17 አመታት ወጣትነታቸውን ለትግል ሃሳባቸው ሰውተው ጫካ የከተሙ ሌላ ታጋይዎች የህዝቡን ልብ አሸንፈው ስልጣን ሲይዙ ሀገራችን ሊብራል ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ሆና ብቅ ብላለች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የብዙሃን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር ማለቅ መቆሙ፣ አንጻራዊ የኢኮኖሚ ለውጥ መመዝገቡ እና በዲፕሎማሲው ዘርፍም እንደ የአባይ ግድብ ማስጀመርና እና የአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫነትን ማስቀጠል ያሉ ዉጤቶች ተመዝግበዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የማዕከላዊ መንግስቱ ተቋማት በአንድ ብሄር ብቻ መያዝ፣ በክልሎች መካከል ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ እድገት መኖር ሌሎች ላይ የመገፋት ስሜት የፈጠረ መሆኑ፣ ነጻ የሃሳብ ዝውውር መታገዱ፣ የህዝብ ጥያቄወችን ከመመለስ ይልቅ ለማፈን የሚደረጉ መንግስታዊ ጥረቶች እና ገፍተው የሚሞግት ሃሳብ ይዘው የሚመጡ ሰዎች መሰወር፣ መታሰር፣ መሰቃየት እና መሰደድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መጥቶ ለውጥ አስፈልጓል። በዚህም ከ 2011 ጀምሮ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ የተደሰተበት እና ተስፋ ያደረገበት “ለውጥ” የተሰኘው ጊዜ ላይ ተደርሷል። ቢሆንም ግን ለውጡ ብዙሃኑ ተስፋ እንዳደረጉበት የእኩል ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት ሳይሆን በየቦታው ግድያ፣ ዝርፊያ፣ ጦርነት፣ ርሃብ፣ መፈናቀል እና የቤተእምነቶች መፍረስ እና ቃጠሎ የእለት ተእለት ዜናችን ሆኗል ።

ታዲያ የዚህ ሁሉ ምንጩ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ የሁሉም ሲሆን በብዙ ሰው ጭንቅላት ውዲያው የሚመጣው መልስ የኢትዮጵያ ህዝቦች የተለያዩ ብሔሮች ወይም ሀይማኖቶች ተከታይ ስለሆኑ እና አብረው መኖር ስለማይችሉ ወይም ስለሚጠላሉ የሚል ነው።ለዚህም ይመስላል ብዙ ሰው አብዮቱ ይዞት በተነሳው ጥያቄ መሰረት መልስ ሆኖ የመጣውን “የብሄር ፌደራሊዝምን” እንደ ችግር አድርጎ መመልከቱ።አሁን ባለው ነባራዊ ሃቅ መሰረት የብሄር ፈደራሊዝም በሃገራችን በሁለት ጽንፍ ይታያል አንደኛው ጽንፍ ያለ ብሄር ፈደራዝም ሃገሪቷ ትፈርሳለች የሚል ሲሆን ሌላኛው ጽንፍ ደግሞ ሃገሪቱ አሁን ላለችበት ችግር ሁሉ መሰረቱ የብሄር ፌደራሊዝም ነው ስለዚህ ሀገራችንን ለማዳን ፌደራሊዝሙ በሌላ አይነት ብሄር ተኮር ባልሆነ ፌደራሊዝም መቀየር አለበት የሚል ነው። እኔ በሁለቱም ሃሳብ አልስማማም ምክንያቱም አንደኛ ነገር ሀገሪቱ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ሃገር እንደመሆኗ ከብሄር ፌደራሊዝም የተሻለ ሊስማማት የሚችል ፌደራሊዝም አይኖርም፤ ምክንያቱም ስርአቱ ህዝቦች በማንነታቸው እንዲኮሩ፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን እና እሴታቸውን እንዲያሳድጉ እና ወደ ሃብት ቀይረው እንዲጠቀሙ መልካም እድል የሚፈጥር ነው። ከዚህ በተጨማሪም አንድን ማህበረሰብ ስለ ማንነትህ እርሳው እና በመልክዐምድራዊ አቀማመጥ የተዋቀርክ ዜጋ ብቻ ሁን ስለተባለ ብቻ ሰላም ሊመጣ አይችልም:: ይልቁንም እንደገና መልሰን ከዜሮ እንድንጀምር እና የባሰ ግጭት ውስጥ እንድንገባ የሚያደርገን ይሆናል። ነገር ግን ደግሞ የብሄር ፌደራሊዝሙ ላይ መቀየር ያለባቸው ነገሮችም እንዳሉ በጣም ግልጽ እና አፋጣኝ ጉዳያችን ነው። ይህን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ያስገቡ እና አሁን ላለንበት ችግር መፍትሄ ሲሆኑ የሚችሉ ሁለት ሃሳቦች አሉኝ።

1) ስለዚህ የብሄር ፌደራሊዝምን ከሃገር በቀል እውቀት ማቀናጀት ትኩረት ልንሰጠው ይገባል ማለት ነው:: እንደሚታወቀው ከአብዮቱ በፊትም በተለያዩ ጊዜ ቀደምት አባቶች እና እናቶች በገባቸው ልክ የአለምን አስተሳሰብና ርዕዮተ አለም ተቀብለው ለሀገር ግንባታ እና ለህዝብ አስተዳደር ተጠቅመውበታል። ነገር ግን ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሀሳቦችን ከባዕድ ሀገራት ቢዋሱም እንኳን ከተዋሱበት ሀገር በተሻለ አሳድገው እና አዳብረው፤ የእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል የእለት ተእለት የህይወት አካል አድርገው ዘመንን አሻግረው የማቆየት ልዩ ተሠጥኦ አላቸው። አሁንም እኛ በዘመናችን የምንጠቀምባቸውን እንደ ዲሞክራሲ እና የብሄር ፌደራሊዝም የመሰሉ ርዕዮተ አለሞች እና ሃሳቦች አንደኛ እራሳችን በደንብ መረዳት እና በተረዳነው ልክ ደግሞ ለማህበረሰቡ በማስረዳት ነገሮችን ተሳስቶ በመረዳት ከሚመጣ ቀውስ ህዝቡን መጠበቅ አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። በተጨማሪም እነዚህ አዳዲስ ሃሳቦች ወደ ማህበረሰቡ የሚሰርጹበትን፣ እንግዳ ሃሳብ ከመሆን የሚወጡበትን፣

ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙ የራሱ ስርዐት እና ወግ ባህል ወደ መሆን የሚያድጉበትን እና ከማህበረሰቡ እሴት ጋር የሚዋሀዱበትን መንገድ ጥናት እና ምርምር በማካሄድ። በአጠቃላይ የኢትዮጲያን ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ጠብቆ ምዕተ አመታትን የሚያሻግር የበኩላችንን ማህበረሰባዊ ስርዐት በጊዜያችን መስራት ይጥበቅብናል። ለዚህም የብሄር ፈደራሊዝሙ የታሰበበትን የ1960ውን የተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ሀሳብ እና አሁን ላይ የደረስንበትን በማየት ምን ላይ እንደተሳሳትን ለመረዳት መሞከርን እንደ አንድ እርምጃ ልንወስደው እንችላለን:: ማለትም በወቅቱ የብሄረሰቦች እኩልነት እና የአንድ ብሄር ጭቆና እንዲቀር የተደረገ ትግል እንደነበረ ሁላችንንም የሚያስማማ ጉዳይ ቢሆንም ሃሳቡ ግን አሁን ላይ እንዳለው ብሄር ብሄረሰቦች እርስ በእርሳቸው በጥርጣሬ እንዲተያዩ እና የአንዱ ብሄር የበላይነት በየጊዜው በሌላው እየተተካ “ሱማሌ ነው ረግጦ ሚገዛሽ”፣ “አፋር ነው ረግጦ ሚገዛሽ”፣ “ሃመር ነው ረግጦ ሚገዛሽ” ወዘተረፈ. እንድንባባል አልነበረም። ይሄንንም በቀላሉ በጊዜው የነበሩ ሃሳቦች ከሚንጸባረቁበት ጹሁፎች መካከል አንዱ በሆነው የዋለልኝ መኮንን ***“on the question of nationalities”*** ከተሰኘው ጹሁፍ ላይ መረዳት እንችላለን በጹሁፋ ላይ ዋለልኝ ***“….it is not only the right but the duty of the most conscious nationality to first liberate itself and then assist others in the struggle for total liberation.”*** ማለትም አጠቃላይ ሃሳቡ ሲተረጎም በተሻለ ንቃተ ህሊና ላይ የሚገኝ አንድ ብሄር መጀመሪያ የራሱን መብት እና ጥቅም ካስከበረ በኋላ ሌላውን ብሄርም መብቱን እና ጥቅሙን እንዲያስከብር ማገዝ ወይም መርዳት ሃላፊነቱ ብቻ ሳይሆን የሞራል ግዴታውም ጭምር እንደሆነ ነው የሚገልጸው። አንዱ ብሄር ለሌላው አጋዥ እና ደጋፊ እየሆነው አብሮ በማደግ ጠንካራ ሀገር መፍጠር በሚል ሃሳብ የተቃኘ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። ስለዚህ የብሄር ፌደራሊዝምን ሃሳብ በደንብ መረዳት እና ግንዛቤ ማስጨበጥ ቁልፍ ጉዳይ ነው።

2) ማዕከላዊ የፌደራል መንግስቱ የሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች እና ብሄሮች የጋራ ተቋም እና የእኩልነት ዋስትናቸው እንጂ የአንድ ብሄር የበላይነት እና በቀል ማስፈጸሚያ መሆኑን ማቆም መቻል ሲሆን ይህም የሚተግበረው መንግስት የቡድን እና የግለሰቦችን ሰብዐዊ መብቶች በተመጣጠነ መልኩ መጠበቅ እና ማክበር እንዲሁም ማስከበርን በፖሊሲ ደረጃ ቀርጾ ሲሰራበት ነው። ይህም ማለት የብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦችን ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ በቋንቋቸው የመግባባት፣ የመማር እና የመስራት መብት የሚያስከብር በዛው ልክ ደግሞ የግለሰቦችን ከቦታቦታ የመንቀሳቀስ፣ የመኖር፣ የመስራት እና ንብረት የማፍራት መብትም የሚያስጠብቅ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ያስፈልጋል ማለት ነው። አሁን ላይ የምናየው ቀውስ በብሄር ስም የተደራጁ ሰዎች የሚፈጽሙት ቢሆንም እንኳን የመንግስትንም የዜጎቹን ሰብዐዊ መብቶች ማስከበር ያለመቻል የሚያሳይ ነው። አንድ አማራ ወይም ኦሮሞ የሆነ ዜጋ የኢትዮጵያ ግዛት እስከሆነ ድረስ ወደ ሌላ ክልል ገብቶ በመኖር፣ በመስራት እና ንብረት በማፍራቱ ለሌላው ብሄረሰብ ስጋት ወይም የመብት ጥሰት ሊሆን የሚችልበት መንገድ መኖር የለበትም። የአካባቢውን ቋንቋ ማወቅ: የአካባቢውን ባህል እና እሴት ማክበር እና መጠበቅ የማህበረሰቡን የቡድን መብት ከማክበር አንጻር ግዴታው ይሆናል። ከዚህ አልፎ ግን ዘሩ እና አጥንቱ ተቆጥሮ የሚገደል ከሆነ መንግስት እንደ ዜጋ ለመብቱ ሊቆምለት እና ሊከላከልለት ይገባል። ስለዚህ ሁለቱ ጽንፎች ወደ መሃል መጥተው የቡድን መብት እኩል ይሆናል የግለሰብ መብት ወይም ደግሞ በሌላ አባባል የዜጎች መብት እኩል ይሆናል ከብሄረሰቦች መብት ወደሚል የጋራ መግባቢያ መምጣት አለባቸው። በመሆኑም የግለሰቦችን መብት የሚደፈጥጥ የብሄር ፌደራሊዝም ልክ እንዳልሆነው ሁሉ የብሄርብሄረሰቦችን መብት የሚደፈጥጥ ሌላ አይነት ፌደራሊዝምም ልክ ነው ብየ አላምንም። የቡድን መብቶችን ከግለሰባዊ መብቶች ጋር አመጣጥኖ መምራት እና ሰላም ማምጣት የሚቻለው ማዕከላዊ ተቋማት በሙያ ስነምግባር፣ በሰብዐዊ መብቶች መከበር እና በእኩልነት የሚያምኑ፣ ለህሊናቸው ተገዥ በሆኑ እና በጥብቅ ዲሲፕሊን በሚመሩ ባለሙያዎች ሲዋቀር ነው። እንጂ የክልል መንግስታትም በብሄር ተደራጅተው ማዕከላዊ መንግስቱም ደግሞ እንደዛው ብሄር ተኮር የሚሆን ከሆነ አሁንም ችግራችን መቀጠሉ አይቀሬ ነው። ማለትም በብሄር ፌደራሊዝም ስርዐት ውስጥ ማዕከላዊ መንግስቱ ላይ የሚቀመጡት ከተለያዩ ብሄሮች የተወከሉ ተወካዮች እንደሆኑ፤ እና የመሪነት ስልጣን የሚቆጣጠረውም ያው ከአንዱ ብሄር የሚመጣ ሰው እንደሚሆን እሙን ቢሆንም፤ ማዕከላዊ መንግስቱ ላይ ሲመጣ ግን ለሁሉም እኩል የቆመ እና በጋራ ጠንካራ ሀገር እና መንግስት መመስረት ላይ ያተኮረ መሪ ሃሳብ፣ የማዕከላዊ ፖሊሲ ወይም መመሪያ ከተጠያቂነት ጋር ሊኖር ይገባል ማለት ነው። ያ ካልሆነ ግን እስካሁን እንዳለው በኢህአዴግ ዘመን ‘’ትግሬ ነው ረግጦ ሚገዛሽ’’ እየተባልን አሁን በብልጽግና ዘመን ደግሞ ‘’ኦሮሞ ነው ረግጦ ሚገዛሽ’’ እየተባልን ህዝቡም በቁም ነገር “ቀጥሎስ ማን ቢገዛ ደስ ይልሃል?” እየተባባለ ቀጣዩን ረግጦ ገዥ ተስፋ በመቁረጥ እያማረጠ የማዕከላዊ መንግስቱ በየተራ በእያንዳንዱ ብሄር እየተያዘ ግፍ የሚሰራበት መድረክ መሆኑ ከቀጠለ ሀገሪቱ ተከፋፍላ ትንንሽ እና ደካማ ሀገራት መሆናችን የጊዜ ጉዳይ ይሆናል። እስካሁን ባለኝ መረዳት ደግሞ ማንም የብሄር ማንነቱን የቱንም ያክል ቢወድም ተከፋፍሎ ትናንሽ ሀገራት መሆንን ግን ለማስፈራሪያ ካልሆነ ከልቡ የሚፈልግ እንደሌለ ግልጽ የሆነልን ይመስለኛል። ስለዚህ የክልል መንግስታት ለብሄረሰባቸው መብት የሚቆሙ በውስጣቸው ለሚፈጠር ብሄር ተኮር ጥቃትም ሃላፊነት የሚወስዱ መሆናቸው በህግ ማዕቀፍ በተደገፈ መልኩ መረጋገጥ ሲችል፤ እና በአንድ ብሄር ፍቅርም ይሁን ጥላቻ ያልታወሩ ሀላፊነት የሚሰማቸው፣

ትክክል እና ስህትቱ የማይምታታባቸው ፣ በሁሉም ህዝቦች እኩልነት የሚያምኑ በጥብቅ ዲሲፒሊን የሚመሩ የማዕከላዊ መንግስት ተቋማት መሪዎች እና አገልጋዮች ካሉን የናፈቅንን ሰላም ማግኘት እንችላለን ማለት ነው። ስለዚህ ሀገራችን ላይ በጋራ ስንኖር የማንስማማበት ጉዳይ ባይጠፋም ግን ቢያንስ አንገዳደልም ማለት ነው።

ታዲያ ለዚህ እውን መሆን መንገዱስ ምንድን ነው? ከየትስ እንጀምር? የሚለው ቀጣዩ ጥያቄያችን ሊሆን ይችላል። እኔ በዚህ ጽሁፍ ለማተኮር የወደድኩት ከብዙ መንገዶች አንዱ በሆነው የሙህራን ሚና ላይ ነው። እዚህ ላይ በዘመናችን ያሉት ሙህራን ከቀደምቶቻቸው ብዙ የሚማሩት ነገር ይኖራል ብየ አስባለሁ:: ምክንያቱም ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጲያ መሰረት የሆነውን የ1960ዎቹን የምሁራን ትግል ስናስታውስ አስደናቂው ነገር መንግስትንና ስርዐቱን ተቃውመው "የመሬት ለአራሹ"፣ "የከተማው ድሃ ኑሮ መሻሻል"፣"የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት" እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንግበው በየአደባባዩ የወደቁት፣ የታሰሩት ብሎም የተገደሉት ምሁራን ከራሳቸው ኑሮ አንዳች ጎድሎባቸው አልነበረም:: ይልቁንም አብዛኛዎቹ መደባቸውን ክደው የነበራቸውን የተሳካ የወደፊት ህይወት ለህዝቡ ነጻነት እና የተሻለ ኑሮ መስዋዕት አድርገውት መሆኑ ነው። እነሱ ጥሩ ኑሮ ለመኖር ቢችሉም ለምቾታቸው ሳይሳሱ በየመንገዱ የወደቁ የ1960ዎቹ የትግል ኮከቦች ትግል ስናስብ አብረን ልናሰናስለው የሚገባው እኛ እነሱ ያሰቡት ነገ ውስጥ ነን ወይ ? የሚለውን ነው። የመጀመሪያው የተማሪዎች ንቅናቄ መሠረት ለሀገሬ ምን ላርግላት? እና ህዝባችን ከዚህ የተሻለ ይገባዋል የሚል እሳቤ ነበር።በ1960ዎቹ የነበሩ ተማሪዎች ንቅናቄ ተማሪዎቹ በየአደባባዩ "መሬት ለገበሬው " ሲሉ ለገበሬው አዝነዉለት ፣ ራርተዉለት እና የተሻለ ነገር ይገባዋል ብለዉ ነበር።በአንጻሩ አሁን ላይ ያለው የተማረው ማህበረሰብ በአብዛኛው ራሱን ከማህበረሰቡ በላይ ከፍ አድርጐ እና ጥሩ ነገር በሙሉ ለራሱ ብቻ እንደሚገባ ነው የሚያስበው። እንጂማ በ"መሬት ለገበሬው!" የሀሳብ ከፍታ ቀጥሎ ቢሆን "መንገድ ለገበሬው!" ፣ "መብራት ለገበሬው!" ፣ "ንፁህ ውሃ ለገበሬው!" ፣ "ጤና ጣቢያ ለገበሬው!!" እያለ መቀጠል እና ገበሬው የተሻለ ኑሮ መኖር ነበረበት ።

እናም እስካሁን ያለው የተማረው ማህበረሰብ የአስተሳሰብ ከፍታ በዚያው ቢቀጥል እና ትውልዱ ገበሬው እንዲሁም የከተማ ነዋሪውም አሁን ላይ ያለበትን ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር መፍታት ላይ ቢያተኩር የብሄር ፌደራሊዝም በራሱ ችግርም ባልሆነብን ነበር። በመሆኑም የሀገራችን ገበሬዎች በአሁን ወቅት እየተቸገሩበት ያለውን የመሰረተ ልማት እና ሌሎችም የግብርናው ዘርፍ ኋላቀርነት ችግሮችንም በመቅረፍ ሌላው ቢቀር በምግብ ራሳችንን የቻልን ህዝቦች እንድንሆን ቢያንስ ዘመናዊነትን አውቀው የሸሹት አሚሾች የሚጠቀሙበትን አይነት የእርሻ መሳሪያ እንኳን በዘመኑ የምህንድስና ሙህራኖቻችን ተሰርቶ ለገበሬው ማዳረስ ያስፈልጋል። ለገበሬው ብቻ ሳይሆን በኑሮ ውድነት፣ በስራ ማጣት እና ሌሎች ጫናዎች ለመኖር እየከበደው በየቀኑ ለአእምሮ መቃወስ እና ሌሎች ችግሮች ተጋላጭ የሆነውን የከተማ ነዋሪም እፎይታ የሚሰጠው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መፍትሄዎችን ለማምጣት ቀን ከሌሊት መትጋት የሙህራኑ መገለጫ ሊሆን ይገባል።

ነገር ግን ለሃገሪቱ ችግሮች በባለቤትነት ስሜት መፍትሄ ከማፈላለግ ይልቅ አንዳንዶቹ የራሴ በሚሉት ብሄር ጥቅም ላይ ብቻ አተኩረው ለሃገሪቱ ህዝቦች በአጠቃላይ አብረው የሚኖሩበትን ሃሳብ ከማዋጣት ይልቅ የጥፋቱ ተካፋይ በመሆን፣ አንዳንዶቹም ለህዝብ መፍትሄ የሚሆን ሃሳብ ይዘው መጡ ሲባል በፖለቲካ ኢሊቱ በመዋጥ እና በመቀልበስ፣ አንዳንዶቹም ደግሞ ነገሩ በጣም ተበላሽቷል ይለይለት በሚል ዝምታን በመምረጥ ሌሎቹ ደግሞ ራሳቸው ላይ እና ለራሳቸው የተሻለ ህይወት መፍጠር ላይ ብቻ በማተኮር የሃገሪቱን ችግር እንደሌለ፣ እንዳልተፈጠረ እና እንዳላየ በማለፍ ህዝቡ ካስተማረው ማህበረሰብ ማግኘት የሚገባውን መፍትሄ ሳያገኝ እንዲቆይ ሆኗል። ስለዚህ አሁንም ነገሩ ሳይብስ እና የበለጠ ዋጋ ሳንከፍል ለፖለቲካዊ ችግሮቻችን ምሁራኑ ስልጣን መፈለግ ላይ ያላተኮረ ህዝቡ እንደ አንድ ማህበረሰብ አብሮ ሊያኖረው የሚችል በእውቀት ላይ የተመሰረተ የመፍትሄ ሃሳቦችን ይዘው መምጣት እና ሚዛናዊ ሆነው መገኘት አለባቸው። በመሆኑም ልክ እንደ ቀደሙት ምሁራን የዘመናችን ምሁራንም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ከአሁኑ የተሻለ ጥረት ማሳየት አለባቸው። ሌላው ቢቀር የሚጨበጥ የእውቀት ዉጤት አበርክተን የህዝቡን ህይወት ለማቅለል ባንችል እንኳን ከህዝቡ በሚሰበሰብ ግብር እየተከፈለን የምንሰጠው አገልግሎት ላይ እንኳን ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን አንሰራፍተን የህዝቡን ህይወት ከማክበድ ብንቆጠብ ለሃገራችን እና ለህዝባችን እድገት ትልቅ አስተዋጽዖ ማበርከት እንችላለን። ለዚህም በተሳይ ምሁራኑን የሚያፈሩት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ወይም ዩንቨርሲቲዎች ማህበረሰባዊ አገልግሎት መስጠትን ልክ እንደ መመረቂያ ጽሁፍ ሁሉ ቅድመ ሁኔታ በማድረግ ምሁሩ የማህበረሰቡን ችግር እና እምቅ እውቀቶች ጠልቆ እንዲረዳ እና የመፍትሄ ሀሳብ እንዲያፈላልግ እድሉን በመስጠት ምሁራን ለማህበረሰቡ ችግሮች የራሳቸው የሆነ አዳዲስ መፍትሄዎችን ማፈላለግ እና መፍጠር የመማራቸው ዉጤት ሊሆን ይገባል።

በአጠቃላይ በእኔ እምነት ለዚህ ሁሉ ምስቅልቅል መፍትሄው የምሁራኑ መመለስና ማህበረሰቡን ከመውቀስ ወጥቶ ራሱን በመገምገም እና በማረም፤ እያነፃፀረ ማህበረሰቡን ከሚያጣጥልበት የሌላ ማህበረሰብ መዋቅር አንፃር እራሱንም በማነፃፀር እኔ ለማህበረሠቤ ምን ማድረግ እችላለሁ? እንዴት ሃላፊነቴን መወጣት እችላለሁ? የሚለውን በጥልቀት ማሠብና ችግሮችን የተጨማሪ ሠው ደም ሳይፈስ መፍታት በሚቻልበት መንገድ ላይ በተጨባጭ መስራት።

በየተሠማራበት የሙያ መስክ ለሀገሩ ሠላምና እድገት የሚጠበቅበትን የሙያ ግዴታውን መወጣት አለበት ። ለዚህም ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የእኔ በሚል እሳቤ እና በባለቤትነት መንፈስ መመልከት፣ ለእራሳችን ግልፅ መሆን፣ በሀላፊነት እንደ ሙያችን ችግር ፈቺ በመሆን ሀገራችን እና ማህበረሰባችን ከውጭ ጥገኝነት የሚያላቅቅ አበርክቶ ለማድረግ መጣር። እና ለትውልድ የሚሻገር ስራ መስራት ዋና እና አበይት ጉዳያችን መሆን አለበት። በመሆኑም ድፍረት፣ ፅናት እና ርህራሄ ከቀደሙት ሙህራን በመውረስ፤ እኛ እነሱ እንዳለሙት የተሻለችውን ኢትዩጵያ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ለመስጠት መትጋት አለብን። ይህም አዳዲስ ሀሳቦችን ከአገር በቀል ትውፊቶች ጋር በማዳቀል፤ የኢትዩጵያዊነትን መሠረት ያልቀቀ ሽግግር በማድረግና፤ ሀገርን እንደ ሀገር ያቆሙ አብሮ የመኖር እሴቶችን ትኩረት በመስጠት፤ ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ ጠቀሜታቸውን የሚያጎላ ጥናቶችን ፣ምርምሮችን እና ማህበረሠባዊ ሙከራዎችን በማድረግ፤ ትውልዱ በተለይም የተማረው ሀይል ለሀገሩ እና ለወገኑ ክብር እና ፍቅር እንዲኖረዉ ማድረግ ለነገ የማይባል ስራ ሲሆን፤ ለዚህም አዎንታዊ እና መልካም ሀሳቦችን መጀመሪያ በራሳችን ቀጥሎም በማህበረሰቡ ላይ በማሳደር ሊተገበር ይገባል ።

## ላመስግነው ነጋልኝ: ሁሉንም የሚወክል ፕሬዘዳንት፣ የእያንዳንዱ ድምጽ የሚሰማበት ምርጫ : የአስተዳደርና የምርጫ ሥርዓት ማሻሻያ በኢትዮጵያ ያለውን አውራ-ብሔር ሥርዓትን እና ያመጣውን ችግር እንዴት ይቀርፋል?

አማርኛን ብቻ ብሔራዊ ቋንቋ ባደረገው ንጉሣዊ ሥርዓት ውስጥ ለልጆቹ የአማርኛ ስም መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከታየው ቅድመ አያቴ እና ያንን ካስቀጥሉት ልጆቹ፣ እስከ የኦሮሞ ተወላጇ እናቴ ኤርትራ በነበረችበት ጊዜ የተማረችውን የትግርኛ ችሎታ በትግራይና በህወሃት አውራነት በተሞላው የመንግስት አስተዳደር ውስጥ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች የተሻለ አገልግሎትን ለማግኘት ስትጠቀም ማየቴ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአውራ-ብሔር ሥርዓት የህይወታችንን አቅጣጫ መቅረጹን ግልጽ አድርጎልኛል። ዛሬ በአንፃሩ ጓደኞቼ ኦሮምኛ አቀላጥፈው በመናገራቸው ሲጠቀሙ፣ ሌሎች ደግሞ ቋንቋውን መናገር ባለመቻላቸው በመንግሥት መዋቅር ውስጥ እንቅፋት ሲገጥማቸው፤ በኢትዮጵያ ያለው አውራ-ብሔር መር የመግስታት ሥርዓት ረቂቅ ፅንሰ-ሀሳብ ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም የሚነካ የዕለት ተዕለት እውነታ መሆኑ እየታየኝ ነው።

ዛሬም ድረስ ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ የእኩልነት ጥያቄን በተመለከተ ያለኝን ግንዛቤ ቀርፆል። በኢትዮጵያ ለእኩልነት የሚደረጉ ትግሎች፣ ከአውራ - ብሔር ሥርዓቶች ፣ በማካተት እና በማግለል መካከል ባለ የማያቋርጥ ትግል የተሞሉ ነበሩ። ታሪክን መደሏላ ማየት ወሳኝ ሁነቶችን እንድንማርባቸውና በነሱ ዉስጥ ያሉ የተስፋ ጭላንጭሎችን እንድናይ ይረዳናል።

በሀገራችን ብሔርተኝነትን ለማጥፋት የተደረጉ በርካታ ትግሎች ቢመዘገቡም፣ ከ1960ዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ የበለጠ ጎልተው የሚታዩት ግን ጥቂቶች ናቸው። እነዚህ ወጣቶች ምንም እንኳን የተሟላና ምቹ ኑሮ ቢኖሩም በምቾቱ ለመታለል ፈቃደኛ አልነበሩም። ይልቁንም የሶሻሊዝምን የእኩልነት ህልምን ወደ እውነታ በማሸጋገርና ማንነት በዜግነት ዙሪያ የሸቦ አጥር ወደማይሆንበት ሁኔታ በመቀየር ለተገለሉት የዝምታ ጩኸት ማጉያዎች ሆነዋል (ቃሲም, 1985)። በነሱ የተደረገው የመሬት መልሶ ክፍፍል እና ሁሉን አቀፍ ሥርዓት ትግል የሱናሚ ያህል ሃይል ስለነበረው ንጉስን አስወግዶ ሀገርን ለመለወጥ በቅቷል (ቃሲም, 1985)። ውጤታቸው የሚታየው በገንዘብ ጥቅም ሳይሆን ማንነት በልደት ሰርተፍኬት ላይ ከተጠቀሰው ብሔር ይልቅ በሰውነት ብቻ የተመሰረተ ሲሆን ነው።

የፊውዳሉን ሥርዓት የገረሰሰው የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ዓላማ የመሬት ባለቤትነት ችግርን መፍታት ነበር። መሬትን ለገበሬዎች መልሶ ማከፋፈል ሕግን ከመቀየርና ለገበሬዎች መሬት ከመስጠት አልፎ የሚገባቸውን ኃይልን ያጎናፀፈ ደፋር እርምጃ ነበር። ይህ እርምጃ ግን አብዮቱ ያስከተለውን የእኩልነት ውጤት ለረጅም ጊዜ ማስፈን አልቻለም። የኃሳ፣ የርዕዮተ ዓለም እና የማኅበራዊ ግጭቶች መፈጠራቸው አንድን የሥልጣን ተዋረድ በማፍረስ ብቻ ሁልጊዜ ትክክለኛ አመራር መገንባት እንደማይቻል ያሳያል (ቃሲም, 1985)።

የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች መኖራቸውን ዕውቅና የሰጠው የ1979ኙ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እኩልነትን ለማምጣት ሌላው ጥሩ እርምጃ ነበር። ይህ እርምጃ የእኩልነት መርህን በሕገ መንግስቱ ላይ ማፅደቁ፣ ከቀደምት አግላይ መንግስታት የተለወጡ ነገሮች እንዳሉ ያሳያል (የኢሕዴሪ ሕገ መንግሥት, 1979)። ይሁንና “የአማራው የበላይነት እየቀጠለ ነው” የሚሉና ይሄንንም እንደ ማታገያ የሚጠቀሙ ታጠቂ ቡድኖች ቢንሰራፋም የታለመው ግብ ግን ማይጨበጥ ሆኖ ቀጠለ (ባልቻ, 2007)።

በ1983 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. 1991) የተደረገው የአመራር ለውጥ ለብሔር ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት

በመስጠት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ሞክሯል (ባልቻ, 2007)። ነገር ግን ይህ የሥልጣን ሽግግር የአማራን የበላይነት በትግራይ አመራር በመተካቱ ዋናውን ጉዳይ ሳይቀርፍ በህብረ ብሔራዊ ሃገር ዉስጥ፣ የአውራ ብሔር ሥርዓትን አስቀጥሏል። ይህም በሚያሳዝን ሁኔታ ክልሎችን እና ብሔር ብሔረሰቦችን ለማጎልበት የተነደፈው የፌደራል አወቃቀር የገባውን ቃል ለመፈጸም አለመቻሉን አሳይቷል (ተፈራ, 2019; ቶላ እና ሮዮ, 2022)።

የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክም ይሄንን የአውራ ብሔር ሥርዓትን በሚቃወሙ ትግሎችና ግጭቶች የሚገለጽ ነው። በ'የተቀናጀች አዲስ አበባ ማስተር ፕላን' የተቀሰቀሰው የኦሮሞ ህዝባዊ ተቃውሞ በወቅቱ የነበረውን የትግራይ የበላይነት በኦሮሞ ማንነት እና ባህል ላይ ያደርስ የነበረውን ስጋት መሰረት ያደረገ ነበር (አሰፋ, 2017)።

የኦሮሞ ጸረ-አውራ ብሔር ትግል፣ ጥብቅ ያልሆነ ማዕከላዊ መንግስት ኖሮት ጠንካራ ክልሎች ያሉትን ፌደራላዊ ሥርዓትን ከመፍጥር እስከ ሙሉ ሉዓላዊነት ድረስ ለተለያዩ ዓላማዎች ሲታገል ቆይቷል። ይሁን እንጂ ከ2007- 2010 የነበረው ምዕራፍ የተለየ አካሄድን ወስዷል። አዲሱ አካሄድ በዋናነት ጉልህ ለውጦችን ከማድረግ ይልቅ ባለው ሥርዓት ውስጥ ማሻሻያዎች ማድረግ ላይ ያተኮረ ነበር (ጃዋር, 2023)። ይህ የስትራቴጂ ለውጥ በ2010 ዓ.ም የኦሮሞ ተወላጅ መሪ መድረኩን እንዲይዝ በማድረግ የፖለቲካውን አካታችነት ጥያቄ መመለስ በማስቻሉ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል።

ቢሆንም፣ የለውጡ ንፋስ ብዙም አልቆየም። ለውጡ የትግራይ መሩን የአውራ-ብሔር ሥርዓት ለመናድ ያለመ ነው ቢባልም፤ ብዙዎች በተለይ የአማራ ፖለቲካ ልሂቃን የትግራይ የበላይነት በኦሮሞ የበላይነት ተተክቷል ይላሉ (ተዘራ, 2021)። ይህ ቅሬታ አሁንም ሀገሪቱን እያስጨነቀ ያለ ሌላ ግጭት እንዲፈጠር ገፋፍቷል።

እንደ ሄሬ እና ባልደረቦቹ Herre et. al. (2023) ዘገባ፤ ከ2012-2014 ዓ.ም በትግራይ የተከሰተው ግጭት ያስከተለው ሞት በዓለም ላይ እጅግ ብዙ ሰው ካለቀበት ከሩዋንዳው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ቀጥሎ ይመደባል። የትግራይ አመራር ግጭቱን የፌደራሊዝምን ህልውና ለማስጠበቅ ገባሁበት ቢልም፤ የአማራ ሃይል ሊያንሰራራ ይችላል የሚል ስጋትም ነበረው። በዚህ ረገድ የጸረ-አውራ ብሔር ትግል ለግጭቱ መባባስ ምክንያት እንደሆነ መጥቀስ ይቻላል።

በትግራይ የተከሰተው ግጭት መቋጫ እንዳገኘ፤ በ2015 ዓ.ም የአማራ ተወላጆች በኦሮሞ የበላይነት የተያዘው መንግሥት ላይ ያደረባቸው ስጋት ሌላ የትጥቅ ትግልን አስነስቷል። በዚህ ዙር አለመግባባቱን ያስከሰቱት የወቅቱ የፖለቲካ ምኅዳር መሠረት የሆነው ሕገ መንግሥቱና የብሔር ተኮር ፌዴራላዊ ሥርዓት ሲሆኑ፤ ሁለቱም የአማራ ሕዝብ የስቃይ ምንጭ ተደርገው ተወስደዋል።

በእነዚህ ተከታታይ ግጭቶች የተወሰዱ ሶስት የተለያዩ መንገዶች አሉ። የመጀመሪያው ፌደራሊዝምን ያማከለ አስተዳደራዊ ማሻሻያ ማድረግ፣ ሁለተኛው አሁን ባለው የፌደራሊዝም ሥርዓት ውስጥ ችግሮችን ለመፍታት ለዘብተኛ ማዕከላዊ መንግሥትን መመስረት ሲሆን ሶስተኛው ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትን በመመስረት ብሔርን መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝምን ማፍረስ ነው። ሆኖም ሦስቱም አካሄዶች የመንግሥትን መዋቅር በማስቀጠል ወይም በመቀየር ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው። ነገር ግን እነዚህ አካሄዶች የመንግሥት መዋቅር ችግሮችን እንደ ብቸኛ የማብራሪያ ስለሚጠቀሙ ሌሎች ወሳኝ ምክንያቶችን ችላ ይላሉ። ታሪካችን እንደሚያሳየው የቀድሞው አሃዳዊ ሥርዓትም ሆነ አሁን ያለው ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የአውራ ብሔር ሥርዓትን ውጤታማ በሆነ መንገድ አልቀነሱም። ይህ የሚያመለክተው የመንግሥትና ሀገራዊ የመዋቅር ሽግግሮች አንዱን አውራ ብሔር በሌላ ቡድን ብቻ የሚተካበት ሥርዓት ውስጥ መጠመዳችንን ነው። ስለዚህም ሀገራዊ መዋቅርን መለወጥ ላይ ከማተኮር ውጪ አማራጭ መንገዶችን መፈለግ ወሳኝ ነው።

## አስተዳደራዊ ግምገማ: የአውራ-ብሔር ሥርዓትን ለመስበር የሥርዓት ማሻሻያዎች ሚና

የኢትዮጵያውያንን የእኩልነት እና ፍትሐዊ ውክልና የማግኘት ጥማትን ለማርካት፤ ይህ ጽሁፍ ሁለት አቅጣጫ ያለው መፍትሄን ያቀርባል። ይህም ዲሞክራሲን ማስፈን አስፈላጊ እንደሆነ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ ቅይጥ የምርጫ ሥርዓትን ተከትሎ ወደ ከፊል ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት መሸጋገር ነው።

## በጠቅላይ ሚንስቴር-ፕሬዝዳንታዊ ቅይጥ ሥርዓት አማካይነት የኢትዮጵያን አንድነት እና እድገት ማስፈን

ይህ አካሄድ ፕሬዚዳንቱ በቀጥታ በምርጫ የሚመረጡበት እና ፓርላማው ብቻ ካቢኔን የማሰናበት ሥልጣን ያለውን (ሴዴሊየስ እና ሊንዴ, 2018) ከፊል ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓትን በመደገፍ፤ ሁለት ራስ ያለው አስፈፃሚ አካልን ይጠቀማል። ሥርዓቱ በፍፁም አብላጫ ድምፅ የሚመረጥ ፕሬዚዳንትን፣ ጠቅላይ ሚኒስትርን እና ተጠሪነቱ ለፓርላማው የሆነ ካቢኔን ያጠቃልላል። ከዚህም በላይ፣ የሚመረጠው ፕሬዝደንት በየክልሉ ድጋፍ እንዲኖረው ለማድረግ ከሁሉም የሀገሪቱ

ክልሎች ቢያንስ የ20% ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል።
እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል፣

**ቀጣይነት እና ትውውቅ:-** ከፊል ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት ከፓርላሜንታዊ ሥርዓት ጋር ሲወዳደር ሥር ነቀል ሽግግር አያስፈልገውም። ኢትዮጵያ ከ1979 እስከ 1987 ፕሬዚዳንቱ በፓርላማ የሚመረጡበት ሥርዓትን ብትከተልም፤ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መዋቅር ነበራት (የኢሕዴሪ ሕገ መንግሥት, 1979; የሽግግር ቻርተር 1983)። የዚህ አይነቱ ልምድ ባለፈ ታሪካችን መኖር አተገባበሩን ቀላል ስለሚያደርገው የህዝብ ተቀባይነትን ሊያስገኝ ይችላል።

**ሕጋዊነት እና ተጠያቂነት:-** በቀጥታ የተመረጠ ፕሬዝዳንት በአንድ የምርጫ ቀጠና ወይም ገዥ ፓርቲ ብቻ ከተመረጠው ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ሲወዳደር ጠንከር ያለ የህዝብ ሥልጣን እና የተጠያቂነት ስሜት ይኖረዋል። ይህም፣ ተጠያቂነትን ለአውራ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን ለመላው መራጭ ህዝብ ስለሚያዘዋውር ሀገራዊ አንድነትን ያዳብራል (ጌታቸው, 2017)።

**አካታችነት:-** የፕሬዚዳንቱ ቀጥተኛ ምርጫ የበርካታ ብሔረሰቦች ድጋፍን ስለሚጠይቅ፤ የተለያዩ አመለካከቶችን በማካተት እና የጎሳ ዝንባሌዎችን በመቀነስ አካታች ፖሊሲዎችን ያበረታታል። ይህም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ችግር ከሆነውን የአውራ-ብሔር ወጥመድ ለማምለጥ ትልቅ ሚና ይኖረዋል (ዋለ, 2017)።

**ሚዛናዊ የሥልጣን ክፍፍል:-** በቀጥታ የሚመረጡት ፕሬዝደንት ጉልህ ሥልጣን ቢይዙም፤ በተዘዋዋሪ የሚመረጡት ጠቅላይ ሚኒስትር በሕግ አውጪው እና በአስፈጻሚው መካከል ወሳኝ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ። ይህ የሥልጣን ክፍፍል ሚዛናዊ አሰራርን ያረጋግጣል (ጌታቸው, 2017 ዋለ, 2017)።

**የአውራ-ብሔር ሥርዓትን ይከላከላል:-** የአውራ-ብሔር ሥርዓትን ለመከላከል እንዲሁም አካታችነትን ለማጠናከር፤ ሁለቱ ዋነኛ ስልጣኖች (ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር) ከተለያዩ ብሔረሰቦች በተውጣጡ ተወካዮች እንዲያዙ ይመከራል።

## ብዝሃነትን ማንገብ: ቅይጥ የምርጫ ሥርዓት ለአካታች ኢትዮጵያ

በፌድራል ሕግ አውጭ አካላት ውስጥ ብሔረሰቦችና ክልሎች ፍትሐዊ ውክልና ቢኖራቸውም፤ አሁን ያለው በምርጫ ጣቢያዎች ለአንድ ዕጩ ብቻ ድምጽ የሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት (first-past-the-post (FPTP)) ጉድለቶችን አሳይቷል። እነዚህ ጉድለቶች የመራጮችን ተሳትፎ በማደናቀፍ የአንድን ፓርቲ የበላይነትን ያባብሳሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ አሸናፊ ሁሉንም ይወስዳል የሚለው ለአንድ ዕጩ ብቻ ድምጽ በሚሰጥበት አካሄድ (FPTP)፤ ለተቃዋሚ እጩዎች የሚሰጥ ድምጽ እምብዛም ለውጥ አያመጣም ተብሎ እንዲታሰብ በማድረግ የመራጮች ተሳትፎን በእጅጉ ይቀንሳል። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በኢትዮጵያ በ2007 ዓ.ም የተካሄደውና አብዛኛውን የተቃዋሚዎች ድምጽ በማባከን ለገዥው ፓርቲ በፌዴራል ደረጃ 100% የፓርላማ መቀመጫዎችን ያስገኘው ምርጫ ነው። በዚህ ምርጫ ለአዲስ አበባ ከተመደቡት 23 ወንበሮች ውስጥ 16 በመቶው የአዲስ አበባ መራጮች ሰማያዊ ፓርቲን የመረጡ ሲሆን፤ 85 በመቶው ለኢህአዴግ ድምጽ ሰጥተዋል። ይሁን እንጂ፣ ኢህአዴግ ያሸናፈው በ100% ነበር። ይህ ሥርዓት የአናሳ ድምጽ መብትን በመንፈግ የመራጮችን ተሳትፎ ዝቅ ስለሚያደርግ ትናንሽ ፓርቲዎች ዘንድ የተስፋ መቁረጥ ስሜት እንዲኖር ያደርጋል (አደም, 2015)።

በሁለተኛ ደረጃ ለአንድ ዕጩ ብቻ ድምጽ የሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት (FPTP) ሥልጣንን በገዥው ፓርቲ በማመቅ የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ያበረታታል። በዚህ የተነሳ በገዥው ፓርቲ ውስጥ አውራ የሆነው ብሔር ወዲያውኑ የሀገሪቱ ፖለቲካ የበላይ ብሔር ይሆንና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማሳደር የፓርላማውን ሚና ለይስሙላ ያደርጋል። ይህም ውክልናን በማደከም የአውራ-ብሔር ሥርዓትን ያጠናክራ (እዮብ, n.d)።

በ2009 ዓ.ም. በገዥው ፓርቲ እና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ቅይጥ የምርጫ ሥርዓትን ለመከተል የተደረገው ስምምነት ለነዚህ ጉድለቶች እውቅና ሰጥቷል። ድርድሩ በዋናነት ያተኮረው የአንድ እጩ ድምጽ አሰጣጥን በማሻሻል ተመጣጣኝ ውክልናን ማስፈን ላይ ሲሆን፤ ከ50:50 ቅይጥ (የተቃዋሚዎች ፍላጎት) እስከ 90:10 ቅይጥ (የመንግሥት ፍላጎት) የነበረው አሰራር ወደ በ80:20 ቅይጥ እንዲቀየር ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር። ነገር ግን ይህ ዕቅድ በመንግሥት ለውጥ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። (ኒያሚን, 2017)።

አሰራሩ ምንም እንኳን ውስን ድክመቶች ቢኖሩትም፤ የሚከተሉት ጥቅሞች ስላሉት ደጋፊዎችን አፍርቷል።

- **አካታችነት:** ቅይጥ የምርጫ ሥርዓት ለሁሉም ፓርቲዎች ጉልህ ውክልና ስለሚሰጥ (ገብረመስቀል, n.d)፤ ትንሽ የህዝብ ብዛት ያላቸው ማኅበረሰቦችም ፍትሃዊ ውክልና እንዲያገኙ ያደርጋል:: ይህም ቀስ በቀስ

የአንድ ፓርቲ የበላይነት እና የአውራ-ብሔር ሥርዓትን ይቀንሳል።

- **የመራጭ ተሳትፎ መጨመር፡-** እያንዳንዱ ድምጽ የዜጎችን ተሳትፎ በማነሳሳት እውነተኛ ፉክክር የሚታይበትን ምርጫ ስለሚፈጥር፤ ዲሞክራሲን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያጠናክራል።
- **የሚባክኑ ድምጾችን መቀነስ፡-** አሰራሩ ሰፊ ተሳትፎን ስለሚያበረታታ፤ አሸናፊ ላልሆኑ እጩዎች የሚሰጡት ድምጾች ለፓርቲያቸው ውክልና እንዲውሉ ይረዳል (ገብረምስቀል, n.d.)።

በመሆኑም አሁን ያለው ለአንድ ዕጩ ብቻ ድምጽ የሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን የሚያደናቅፍ እና ውስብስብ የሥልጣን ሽግግርን የሚያበረታታ ነው። ወደ 50:50 ቅይጥ የምርጫ ሥርዓት መሸጋገር አካታችነት ለማስፈን፣ የመራጮች ተሳትፎን ለመጨመር እና ከአንድ ፓርቲና ብሔር የበላይነት ለመውጣት መፍትሄ ይሆናል።

### መደምደሚያ፡ የአውራ-ብሔር ሥርዓትን በቁርጠኛ አፈጻጸም መቅረፍ

እንደ መፍትሔ ያቀረብኳቸው ከፊል ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓትና ቅይጥ የምርጫ ሥርዓት ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ውይይቶች ሙሉ በሙሉ አዲስ ባይሆኑም፤ ከአውራ-ብሔር ሥርዓት ለመላቀቅ ተግባራዊ አካሄድን ይቀይሳሉ ብዬ አምናለው። ከላይ እንደተገለጸው ከተለያዩ ብሔረሰቦች የተውጣጡ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲኖሩ፤ ሥልጣንን በተቀላጠፈ ሁኔታ በመከፋፈልና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማጎልበት የብሔር ግጭቶችን ይቀንሳሉ።

የቸገረን ውይይት ሳይሆን እነዚህን ማሻሻያዎች ለመተግበር የማያወላውል ቁርጠኝነት ስለሆነ፤ እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት በሕግ አውጭውም ሆነ በአስፈፃሚው አጀንዳ ለእነዚህ ጉዳዮች ቅድሚያ መሰጠት አለበት። ስለዚህ፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ማሻሻያዎች በንቃት እንዲደግፉ አበረታታለሁ፡-

- ሀገሪቱን አንድ ለማድረግ እና የጋራ ጥቅምን ለመወከል የሚሰራ በቀጥታ የሚመረጥ ፕሬዝዳንት
- የአናሳው ድምፅ መሰማቱንና ውክልና ማግኘቱን የሚያረጋግጥ ቅይጥ የምርጫ ሥርዓት

ነፃና ፍትሃዊ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ከቁርጠኝነት ጋር ተዳምሮ፤ እነዚህ ማሻሻያዎች የአውራ-ብሔር ሥርዓትን በማስቆም፤ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ አካታችነትንና እኩልነትን ያጎናጽፋሉ።

## ሊድያ ዮሃንስ: የዜግነት መብት ጥያቄ የፖሊስ ጭካኔ በተሞላባት ኢትዮጵያ

ዜግነት ከተገዢነት በላይ ሲሆን፣ መንግሥት ሊጠብቃቸው እና ሊያስከብራቸው የሚገቡ መብቶችንም ያጠቃልላል። በአሳዛኝ ሁኔታ፣ የ1966ቱን የተማሪዎች ንቅናቄን ተከትሎ ከተደራጀው የመጀመሪያው የሪፐብሊክ ሥርዓት ጀምሮ፤ እስካሁ ድረስ በኢትዮጵያ ያለው የዜግነት መብት እሳቤ ገና በጅምር ላይ ይገኛል። ይህ ጽሑፍ ከዚህ የዜግነትና የመብት ችግሮች በስተጀርባ ያለው ዋነኛው ምክንያት በመንግሥት ሕጋዊነት ላይ ከፍተኛ ስጋት እየፈጠረ ያለው የፖሊስ ጭካኔ እና የዳኝነት ሥርዓት ኢፍትሃዊነት እንደሆነ ይሞግታል። ጽሑፉ ታሪክን እና የዓለም አቀፍ ተሞክሮን በመጥቀስ፤ እንደ የንብረት መብትን ጥሰት፣ በህይወት የመኖር መብት ጥሰት እንዲሁም ከስቃይ የመጠበቅ እና ፍትሀዊ የፍርድ ሂደት የማግኘት መብትን የመሳሰሉትን አንገብጋቢ የፖለቲካ ችግሮች የመፍታትን አስፈላጊነት ይሞግታል።

ዛሬ በዓለማችን ተገዢነት በኅብረተሰብ እና በመንግሥት መካከል ያለ መሰረታዊ ግንኙነት ነው የሚለው ሀሳብ በጭራሽ አይሰራም። የመንግሥት ስልጣንን መሰረት ያደረጉ ታላላቅ አብዮቶች እና ታሪካዊ ክስተቶች መከሰታቸው የፖለቲካ ቅቡልነት ከህዝብ ይሁንታ የሚመጣበትን ሁኔታ ፈጥሯል። ይህ ስምምነት መንግሥት ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱ ላይ የሚያጠነጥን ነው። ከእነዚህ ኃላፊነቶች መካከል ዋነኞቹ በህይወት የመኖር መብትን ማስጠበቅ፣ ከስቃይ መከላከል፣ የንብረት መብት ማስከበር እንዲሁም ፍትህ የማግኘት መብትን ጨምሮ የዜጎች መብቶችን ማስጠበቅ ናቸው። እነዚህ መብቶች በመንግሥት እና በኅብረተሰቡ መካከል ላለው ግንኙነት መሰረታዊ ስለሆኑ የመንግሥትን አፈፃፀምን ለመገምገም እንደ መስፈርት ሲያገለግሉ ይችላሉ። በታሪክም ሆነ በአለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደታየው፤ መንግሥታት ዜጎቻቸውን መጠበቅ ሲያቅታቸው ዜጎችን ከመጉዳት ባለፈ የመንግሥትን ቅቡልነት አደጋ ላይ ይጥላሉ።

መንግሥታት ምንም ያህል ሃብታም ቢሆኑም የቅቡልነት እጦትን አቅልለው ማየት የለባቸውም። በዚህ ረገድ ከሮድኒ ኪንግ እና ጆርጅ ፍሎይድ በአሜሪካ፣ በፈረንሳይ በፖሊስ ከተገደለው ናሄል ሜርዙክ፣ በእንግሊዝ በአሸባሪነት ተጠርጥሮ ከተገደለው ዣን ቻርለስ ዴ ሜኔዝስ እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በኬንያ ውስጥ በፖሊስ የተገደሉት 15 ሰዎችን ስንመለከት በዜጎች አለመታመን ምን ያህል አስፈሪ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በመንግሥት እና በዜጎች መካከል ጥሩ ግንኙነት አለመኖሩ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ድጋፍ ያሳጣዋል፡፡ እንደሚታወቀው የሕዝብን ፍላጎት የማይቀበል መንግሥት ብዙም ድጋፍና ተቀባይነት የማያገኝ ሲሆን፤ መንግሥት የግብር መክፈልን አስፈላጊነት በሚመለከት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ የወጣባቸው ማስታወቂያዎች ከማሰራት ይልቅ መልካም ገጹ ላይ ቢሰራ በአንፃራዊ የዜጎችን ንቁ ድጋፍ ማሳደግ ይችላል። ኅብረተሰቡ በፍትህ ተቋማት ላይ ያለው እምነት ወንጀልን ለመቀነስ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ትልቅ መፍትሔ መሆኑንም ጥናቶች አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ግሎባላይዜሽን በከፍተኛ ሁኔታ በተስፋፋበት ዓለም አንድ መንግሥት ከሌሎች ሀገራት መንግሥታት ጋር ያለው ተቀባይነት እንደ የኃይል መለኪያ ተደርጎ ይወሰዳል። ታሪክ እንደሚያሳየው ለሰብአዊ መብት ደንታ ቢስ የሆኑ መንግሥታት ከሌሎች መንግሥታት ብዙ ክብርን አያገኙም፡፡ ስለዚህ መንግሥት በሕዝቦቹ ዘንድ ያለው ተወዳጅነት በዓለም መድረክ ላይ ያለውን አቋም ሊያንፀባርቅ ይችላል።

የኢትዮጵያ ሁኔታ ከዚህ ጋር በተያያዘ ብዙ ጉድለቶች ያሳያል። በተማሪው ንቅናቄ ወቅት ዋና ዋና ግለሰቦችን ማሰር እና መግደል - በተለይ የጥላሁን ግዛው ሚስጢራዊ ሞት - ንቅናቄው በይበልጥ እንዲያንሰራፋ እና በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሪፐብሊክ በአፋሳሽ ትግል ቢፈጠርም እስካሁን ድረስ ለሕዝብ የሚጠቅም የመንግሥት ተሞክሮ ተግባራዊ አለመሆኑ አሳዛኝ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ብዙዎቹ ችግሮች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የቀጠሉ ቢሆንም፤ በዜጎች ላይ ግን ተመሳሳይ ምሬት አይታይም፡ ፡ በመሆኑም ከሕዝብ ዘንድ ትግስት ቢኖርም፤ መንግሥት እራሱን ለማሻሻል እና መሠረታዊ መብቶችን ለማስከበር አለመነሳሳቱ ያሳዝናል።

አዲሱ አመራር ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በ'ማዕከላዊ' ማረሚያ ቤት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንዲሁም የፍትህ ሴክተር ማሻሻያዎችን በተመለከተ ቃል የተገቡ ጉዳዮች ላይ መሻሻሎች ይደረጋል ተብሎ ይጠበቅ ነበር። አለመታደል ሆኖ ግን በዚህ ረገድ ምንም ዓይነት ጉልህ እመርታ አልመጣም፤ እንዲያውም ሁኔታዎች የተባባሱ ይመስላሉ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2020፣ 2022 እና 2023 የነበረውን የኢትዮጵያ የፕረስ ነፃነት ደረጃን ስናነፃፅር ከ99ኛ ወደ 114ኛ እንዲሁም በመጨረሻ ከ180 ሀገራት ወደ 130ኛ ዝቅ ማለቱን ያሳያል። በተመሳሳይ እ.ኤ.አ. በ2020 27 የነበረው 'የታገቱ' የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ቁጥር በ2021 ወደ 30፣ በ2022 ወደ 37 እንዲሁም በ2023 ወደ 48 ከፍ ብሏል።

ነገር ግን አሳዛኝም ከእውነትም የራቀው የሆነው አዲስ ነገር ቢኖር፤ ይህንን ጉዳይ እንደ ብሔር-ተኮር ችግር ለመቅረጽ የተደረገው ጥረት ነው፡፡ እውነታው ግን የየትኛውም ብሄር ተወላጆች ሃሳባቸውን በመግለጻቸው ብቻ እየታፈኑና እየተሰቃዩ መሆናቸው ነው። ገጣሚ በላይ በቀለ ወያ፣ ጃዋር መሀመድ፣ እስክንድር ነጋ እንዲሁም ሌሎች ምንም አይነት ማብራሪያ ሳይሰጡ የጠፋባቸው በርካታ አጋጣሚዎች ለዚህ ማሳያ ይሆናሉ። በተጨማሪም ተወዳጁ የየኛ ሚዲያ አዘጋጅ ንጉሴ ብርሃኑ እንዲሁም አክቲቪስት እና የታሪክ መምህር የሆነው ታዬ ቦርኬና በፖሊስ ታግተው ከድብደባ በኋላ የተመለሱበትን አጋጣሚ መመልከት እንችላለን። አንጋፋው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ስለመከላከያ ሰራዊቱ ጽፏል በሚል ከ5 ወራት በላይ መታሰሩም ሌላው ዋነኛ ማሳያ ነው።

ስጋቱ ከግለሰቦች አልፎ የንብረት መብታቸውንም ይነካል። ፖሊሶች የተከሳሽን/የተጠርጣሪን ንብረት ሲታሰሩ ይይዙ እና ግለሰቦቹ ክሱ ከተነሳላቸው በኋላ ለማስመለስ ሲጠየቁ ምንም አይነት ትብብር አልሰጥም ያሉበት ሁኔታ ስፍር ቁጥር የለውም። ብዙውን ጊዜ ወይ ንብረቱ በፖሊሶች ይወስዳል ወይም በቸልተኝነት ምክንያት ይጠፋል። ፖሊስ ህዝቡን ከመጠበቅ ይልቅ ኅብረተሰቡን የማጥቂያ መሳሪያ በመሆኑ፤ ቀድሞውንም ለችግር የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለከፋ ደረጃ ተጋልጠዋል። ሕግ አስከባሪዎች በአብዛኛው ገንዘብ ስለሚገዛቸው መብቶች በፍጥነት ከአቅም በላይና ውድ ወደሆኑ ሸቀጦች ተለውጠዋል።

በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ እነዚህ ክስተቶች ተጠርጣሪዎች በ48 ሰአታት ውስጥ ክስ ካልተመሰረተባቸው እንደለቀቁ የሚለው ሕግ እንደ ተራ ምክረ ሃሳብ ተወስዶ ጉዳያቸው ለአመታት ፍርድ ቤት ሳይታይላቸው በእስር ላይ ከሚገኙት በርካታ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ጉዳይ መሆኑ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የአንድ ሰው መታሰር ሲሰማ "በፖሊስ እጅ አትውደቅ ምክንያቱም ከታሰርክ መውጫ የለህም" የሚለው አነጋገር የተለመደ ሆኗል። ታዲያ መንግሥት በእውነት ዜጎቹን እያገለገለ ነው? ግለሰቦችን በዘፈቀደ በጥቃቅን ጥፋቶች ለረዥም ጊዜ ማሰር ደህንነትን ከማረጋገጥ ይልቅ የማስፈራራት ዘዴ አይደለምን? ታዲያ ዜግነታችን ምን ማለት ነው? ይህ በንዲህ እንዳለ፣ አሁንም እንደገና በሚያሳዝን ሁኔታ፣ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በፖሊስ ከሚፈጸሙ ግድያዎች ጋር ሲነጻጸሩ ኢምንት ጉዳይ ይሆናሉ። ለእስር እንኳን የማያበቃ ጥፋቶችን ያጠፉ ወጣቶች በፖሊስ በጥይት ተመትተው ተገድለዋል። ይህ በተለይ ግጭት

በሚፈጠርባቸው አካባቢዎች እንደ ‘ምክንያታዊ እርምጃ’ ሊወሰድ ስለሚችል በነዚህ አካባቢዎች በብዛት ይታያል። በቅርቡ በአምቦ ከተማ በሰዓት እላፊ ወደውጭ ወጣ በሚል የ4 አመት ህጻን ላይ የተኮሰው የመከላከያ ሰራዊት አባል ጉዳይ በማህበራዊ ሚዲያ እየተሰራጨ ነው። በተመሳሳይ እዛው አምቦ ከተማዋን ለመቆጣጠር በተደረገው እንቅስቃሴ በፌደራል ታጣቂ ሃይሎች የተገደለው የ13 ዓመት ህጻን ልጅና እጅግ አሳዛኝ በሆነ መልኩ የቆሰለውን ሰላማዊ ወጣት ግድያን ለማበረታታት ‘ጨርሰው’ የሚል ትዕዛዝ የተሰማበት የድምፅ ቅጂ የችግሩን ተጨባጭነት ያሳያል።

ይህ ያለንበት ሁኔታ በጣም አሳዛኝ ቢሆንም መፍትሄ የሌለው ነው ብዬ አላምንም:: ዋናው መፍትሄ ነባሩን እውነታ ችላ ከማለት ወይም ሽፋፍኖ ከማለፍ ይልቅ መጋፈጥ ነው። የማኦ ዚ ዶንግ አብዮት ፅንሰ-ሀሳብ ከዚህ ጋር ተስማሚ ነው። አብዮተ ፅንሰ-ሀሳቡ መንግሥት ፖሊሲዎቹን በየጊዜው እንዲገመግም እንዲሁም ዜጐች እንደ ሀገሪቱ ሁኔታ እና ፍላጎት አብዮቱን እንዲያስቀጥሉ ጥሪ ያቀርባል። ይህ የመብት እጦት በመጪዎቹ 50 ዓመታት ኢትዮጵያን ለሚያንሰራራት ቀጣዩ አብዮት መሪ ሃሳቦች ውስጥ አንዱ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ። ይህንን ለማሳካት መንግሥት ጠንካራ የፖለቲካ ፍላጎት ማሳየት እና ከሕገወጥነት ጋር ተያይዘው የሚመጡትን አደጋዎች መከላከል፣ ምሁራን ውጤታማ አመራር መስጠት እንዲሁም ዜጎች ደግሞ ዝምታቸውን ለስበር ፈቃደኛ መሆን አለባቸው።

***መደምደሚያ***

የፖሊስ ጭካኔ እና ኢፍትሃዊነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ሆኖ መቆየቱ አሳዛኝ እውነታ ነው። ነገር ግን ማኦ እንደሚመክረው፣ ዜጎች እንደዚህ አይነት በደልን መታገስ ወይም መቀበል የለባቸውም። ‘ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ’ የሚለው አባባል የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ስሜትን መወከሉ በጣም ያሳዝናል። ይህ ዝምታ መንግሥት ያለው ሕዝብን ማገልገል እንደሆነ ካለማወቅ የሚመጣ ነው። ሰለዚህ ህዝቦቻችን ማንኛውንም አይነት በደልን በመቃወም አንገታቸውን ቀና እንዲያደርጉ እመኛለሁ። ነገር ግን ይህን ለማሳካት አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ስለሚጐድለን ግንዛቤያችንን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት ማደረግን ይጠይቃል። ይህ ጉዳይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ አስቸኳይ ጉዳይ ባይመስልም፤ የሕግ ማስከበር ጉዳዮችን ለመፍታት ከአሁን ውጭ ሌላ ምቹ ጊዜ ስለሌለ ቀስ በቀስ ሊሠራ ይችላል ብሎ ማቆየት ስህተት ነው። የመንግሥት ሕግ አስከባሪ አካል ለዜጎቹ በፍፁም ስጋት መሆን የለበትም። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በተደረገበት ሀገር ቆመን ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ መቀበል ክህደት ስለሚሆን፣ ለነገ የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት የዛሬው ችግር የመጪው ትውልድ ጨኸት አለመሆኑን የሚያረጋግጥና የኢትዮጵያን ፍላጎት የሚመጥን አብዮት ዛሬ ያስፈልገናል። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መሪዎች “መሬት ላራሹ” ሲሉ ጥሪ እንዳቀረቡት አሁን ደግሞ “መብት ለባለቤቱ” ብለን መነሳት አለብን፡ እንደ 5ኛ አመት የሕግ ተማሪ የዜጎችን መብት ለማስመለስ በሚጥር አብዮት የተቀረጸች ሀገርን ማየት ራዕዬ ነው።

## መሰሉ ብርሌው: የመሬት ባለቤትነት መብትና የግብርና ልማት በኢትዮጵያ

ግብርና ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የመኖር ዋስትና ነው። ግብርና በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አማውራዎች፣ አባውራዎች፣ ወጣቶችና ህፃናት ህይወት መድህን፤ ለሀገራችን ኢኮኖሚም የጀርባ አጥንት እንደሆነ ይታወቃል። ኢትዮጵያም ለግብርና ልማት የተሰጠች እድሜ ጠገብ ሀገር ናት። ሰፋፊ ለእርሻ ተስማሚ የሆኑ መሬቶች፣ በርካታ ወንዞች፣ መልከ ብዙ የመልካ ምድር አቀማምጥና እና ተስማሚ የአየር ንብረት ባለቤት መሆኗ ብዙ አይነት ሰብሎችን እንድታመርት ይስችላታል። ከ 80% በላይ የሚሆነው ህዛቧቿም የ3 ሺህ አመታት ልምድ ያላቸው ገበሬዎች ናቸው::ግብርናው የኢትዮጵያ ወሳኝ የምግብ ፣ የገቢና የስራ እድል መስክ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል:: የቅርብ ግዜ መረጃዎች እንደሚያሳይቱ ሀገራችን ወደ ውጭ ከምትልካቸው ምርቶች መካከል 77 በመቶው የግብርና ምርቶች ናቸው። የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ህልውና የተመሰረተው በግብርና ላይ እንደሆነ እሙን ነው።

ይሁንና የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ በከፍተኛ ችግር የተበተበ ስለመሆኑ ሁሉንም ሰው የሚያስማማ ሀቅ ነው። ምንም እንኳን ላለፉት ሶስት አስርት አመታት የተሸሻሉ ግበአቶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ብዙ ጥረት ቢደረግም በከፍተኛ ቁጥር እያደገ የመጣውን ህዝብ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ አልተቻለም።ግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ተብሎ የሚታወቀው የግብርና ፖሊሲ በ 1994 ዓ.ም ሲነደፍ የግብርናው እድገት ወደ ኢንዱስትሪ ልማት የሚያደርስ መሸጋገሪያ ድልድይ ይሆናል በሚል እሳቤ ላይ ተመስርቶ ነበር። ይህም ማለት ግብርናን በሳይንሳዊ እውቀትና ዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመደገፍ፤ የአመራርት ስልትንና እውቀትን በማሳደግ፤ የግብርና ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ መጠን መጨመረን ታላሚ ያደረገ ነበር። ግብርና በሳይንስና በቴክኖሎጅ ተደግፎ ወደ መካናይዜሽን ሲሸጋገር ምርትና ምርታማነት መጨመር ብቻ ሳይሆን ለግብርና አገልግሎት የሚውለውን የሰው ሀይል በከፍተኛ መጠን ይቀንሳል። በዚህም ምክንያት የተትረፈረፈ የሰው ሀይልና ወረት ይፈጠራል። ይህም ማለት በሜካናይዘድ የታገዙ ጥቂት አርሶ አደሮች

በርካታ የሀገሪቱን ህዝብ የምግብ አቅርቦት መሸፈን ይችላሉ። በዚህም ምክንያት በርካታ አርሶ አደሮች ከግብርናው ዘርፍ በመውጣት ወደ ከተሞች በመሄድ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተቀጥረው መስራት ይጀምራሉ። ይህ ሁኔታም ሰራተኛው ለፍጆታ ምርቶችና ለአገልግሎቶች ያለው የገበያ ፍላጎት መጨመር ከሚካናይዘድ እርሻ መስፋፋትና ለስራው የሚሆኑ ግዙፍ ማሽነሪዎች መጨመር ጋር ተዳምሮ እነዚህን ግብዐቶች የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች እንዲበራከቱና በዘርፉም የሚደረገው ኢንቨስትመንትን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲበረታታ በማድረግ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገትን ያመጣል። ይህም በ18ኛው ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ የተከሰተው ከፍተኛ የግብርና ምርታመነት እንደማሳያ ማቅረብ ይቻላል። ሁኖም ግን ግብርናው እንኳን ሀብት ሊያመነጭ ቀርቶ ሕዝቡን መግቦ ማደር ከተሳነው ሰነባብቷል። የግብርናው ምርትና ምርታማነት በበቂ ሁኔታ አለመጨመር፤ የሕዝብን የምግብና የኢንዱስትሪውን የግብዓት ፍላጎት ማሟላት አለመቻል ምክንያት በርካታ ምሁራን የየራሳቸውን ግምገማና ድምዳሜ ያስቀምጣሉ፡፡ እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ የግሌን ግንዛቤና እይታ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

አስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹ የኢትዮጵያ የለውጥ ወቅት ነበር። ለውጡን የሚመራውና የለውጡ ሀይል የሆነው ወጣቱ ሲሆን በተለይም የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ቀዳሚዎች ነበሩ። ታዲያ በዚያ የለውጥ ወራት ጊዜ የነበረው እንዱና ትልቁ ጥያቄ የመሬት ባለቤትነት መብት ጥያቄ ነበር። በጥቂት የመሬት ከበርቴዎች እየተጨቆነ የሚኖረው ሰፊውና ደሀው ህዝብ በደል ያበቃ ዘንድ ትግሉ ተቀጣጠለ። ይህ የመሬት ባለቤትነት መብት ጥያቄ 1966 ዓ.ም ለፈነዳው አብዮት ዋና ጥንሥስ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ደርግ ስልጣን በያዘ ማግስት የተማሪውን “መሬት ላራሹ” ጥያቄ ለመመለስ ተስማማ። የካቲት 25 ቀን 1967 በታወጀው አዋጅም መሬት የሰፊው ህዝብ እንደሆነ ተደነገገ። ይሁን እንጂ ታዲያ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ተመለሰ ማለት አይቻልም። የመሬት ላራሹ ጥያቄ የገበሬውን የባለቤትነት ጥያቄ የሚመለከት ነው። ደርግ ከፊውዳሉ ነጥቆ ባለቤትነቱን ለህዝብ ሰጠሁ ቢልም ህዝብ የመሬት ባለቤት ነው ለማለት በሆነ መንገድ ተደራጅቶ መምጣት ነበረበት። በመሆኑም በተዘዋዋሪ መሬት የመንግስት ከመሆን አላለፈም። በጠቅላላው አዋጁ ብዙ መሬት ካላቸው ግለሰቦች ላይ መንጠቁን እንጂ ለገበሬዎች መስጠት ላይ በሚገባ አልሠራም፣ ለገበሬውም የተረጋገጠ የመሬት ይዞታ ዋስትና አልሰጠም የሚል ሙግትም ይነሳበታል። የደርግ መንግስት መሬትን ይዞ አስራ ሰባት አመት ከዘለቀን በሁዋላ ኢህአዴግ በትረ-መንግስቱን ተቆጣጠረ። በ1987 ዓ.ም የጸደቀው የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው ሲል ያስቀምጣል። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ሲልም ይደነግጋል። ይህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ የገጠር መሬት በእጁ ያለ ባለይዞታ መሬቱን መሸጥም ሆነ መለወጥ እንደማይችል በግልጽ አስፍሯል። መንግሥቱ ኃይለ ማርያምም ሆነ መለስ ዜናዊ መሬት የሕዝብና የመንግሥት ነው በመባሉ ብቻ ገበሬውን የመሬት ባለቤት አድርገናል ቢሉም ሁለቱም መሪዎች መሬት ለገበሬው ሰጠን የሚሉት ግን ፖለቲካዊ ድጋፍ ለማግኘት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ይህ አካሄድ ገበሬውን ሙሉ ለሙሉ የመሬት ባለቤት (መሬቱን የመሸጠም ወይም የመለወጥ መብት) ካለማድረጉም በተጨማሪ በግብርናው ዘርፍ እድገት እንዱና ዋነኛው ማነቆ ሁኖ ቀጥሏል። ከዚ በታች ገበሬው መሬቱን የመሸጥ፣ የመለወጥ መብታ መከልከሉ በግብርናው ዘርፍ እድገት ላይ ያሳደረውን አሉታዊ ተፅእኖ በአራት መከራከሪያዎች እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የመጀመርያው በግብርናው ዘርፍ ስኬታማ ያልሆነ ወይም ፍላጎት ያጣ አርሶ አደር መሬቱን በመሸጥ በሚያገኘው ካፒታል ስኬታማ እሆንበታለሁ ወደሚለውና ወደሚወደው የስራ ዘርፍ እንዳይቀላቀል መገደቡ ነው። ይኸውም አንድ አርሶ አደር ምንም እንኳ በግብርናው ዘርፍ ስኬታማ ባይሆንና የስራ ዘርፉን ባይወደውም ሌላ የስራ ዘርፍ ላይ ለመስራት የሚሆን መነሻ ካፒታል ስለማይኖረው ካለፍላጎቱ ዕድሜውን ከእጅ ወደ አፍ በሆነው የግብርና ህይወቱ እንዲኖር ያስገድዳል። ይህ ደግሞ የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማነት የሚቀንስ ብቻ ሳይሆን የሌሎቹንም የኢኮኖሚ መስኮች እድገት የሚያቀጭጭ ይሆናል። በሌላ በኩል ያለውን ጥቂት መሬት በሚገባ አለስልሶ አርሶ ጥሩ ምርት የሚያገኝ አርሶ አደር፤ በያመቱ ከግብርናው ያገኘውን ትርፍ ምርት በመሸጥ ትንሽ ወረት ሊይዝ ይችላል። ይህ ገበሬ በግብርና ስራው ውጤታማና በስራ ዘርፉም ደስተኛ ከሆነ ባለችው ትንሽ ወረት ተጨማሪ መሬት በመግዛት ግብርናውን ለማስፋፋትና ምርቱን ለመጨመር ፍላጎት ይኖረዋል። ሁኖም ግን የሀገሪቱ የመሬት ፖሊሲ ይህንን ስለማይፈቅድ የገበሬውን የእርሻ ስራ የማስፋፋት፣ ምርትና ምርታማነት የመጨመር ፍላጎት በመገደብ ጠንካራና ውጤታማ አርሶ አደሮች በብጣሽ መሬት ገድቦ ያስቀራል። ይህ ደግሞ የገበሬዎችን ተጨማሪ ሀብት የማፍራት መብት ብቻ ሳይሆን በግብርናው ዘርፍም ላይ እዚህ ግባ የሚባል እድገት እንዳይመጣ እንቅፋት ይሆናል። እዚህ ጋር የኔን አባት እንደ አብነት ማንሳት ይቻላል። አባቴ ብርሌው አባተ ይባላል። ጠንካራ ገበሬ ነው። ባለችው ሁለት ሄክታር መሬት ላለፋት ከሀያ በላይ አመታታ የግብርና ሙያ ላይ ተሰማርቶ ቆይቷል። ሁኖም ግን የግብርና ግብዐት መሻሻል ከፈጠረው እድል ውጭ በየአመቱ ከሚያገኘው ምርት ላይ እዚህ ግባ የሚባል ልዩነት አይስተዋልም። ልጅ ሁኘ በጣም ይደንቀኝ የነበረውም ይህ ነው፤ አመቱን ሙሉ ጠንክረን ሰርተን የምንገኘው የምርት መጠን ላይ ግን ለውጥ ማምጣት አልቻልንም። አባቴ ምንም ያክል ጠንካራና ሙያውን የሚወድ አርሶ አደር ቢሆንም ቅሉ የሀገራችን የመሬት ፖሊስ ግን ባለችው ትንሽ ወረት ተጨማሪ መሬት ገዝቶ እርሻውን እንዲያስፋፋና ምርቱን እንዲጨምር አልፈቀደለትም። በዚህም ምክንያት በያመቱ የሚያገኘው የምርት መጠን ላይ እዚህ ግባ የሚባል መሻሻል ሳይታይ አመታትን ዘልቋል።

በሌላ በኩል የመሬት ፖሊሲው መሬትን የመሸጥና የመለወጥ መብት ለገበሬው ቢያጎናጥፍ በግብርና ስራው ስኬታማ ያልሆነ አርሶ አደር መሬቱን በመሸጥ በሚያገኘው ካፒታል ይበልጥ ስኬታማ እሆንበታለሁ በሚለው ዘርፍ በመሰማራት (በኢንዱስትሪ ወይም በአገልግሎት ዘርፍ) ህይወቱን ያሻሽላል፤ ለሀገሪቱም የኢኮኖሚ እድገት የራሱን ሚና ይጫወታል። በግብርናው ስኬታማና ደስተኛ የሆነ አርሶ አደር ደግሞ ባለው ወረት የመሬት መጠኑን እያስፋፋ የበለጠ ምርት ያገኛል። ይህም የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ለምግብ ዋስትናም ሆነ ለውጭ ምንዛሬ ገቢ ማስገኛ ያገለግላል። በሌላ በኩል መሬት እንዲሸጥና እንዲለወጥ መፈቀድ የለበትም የሚሉ ወገኖች ሶስት የመከራከሪያ ሀሳብ ያነሳሉ። አንደኛው መሬት ይሸጥ ይለወጥ ተብሎ ቢፈቀድ አርሶ አደሩ መሬቱን ሸጦ ከተማ ይሰደዳል፤ የሚል ስጋት ያስቀምጣሉ። ይህም ፍልሰትን የሚያባብስና የስራ አጥ ቁጥርን የሚጨመር ይሆናል ሲሉ ይሞግታሉ። ሁለተኛው መከራከሪያ ሀሳባቸው ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊና መሰረተ ልማት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች መሬት የግለሰቦች ቢሆን መሰረተ ልማቶችን ለማስፋፋት ግለሰቦች ከፍተኛ ገንዘብ ስለሚጠይቁ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅና ስራውን እንዲጓተት ያደርጋል ባይ ናቸው። ሶስተኛው መሬትን መሸጥ መለወጥ እንዳይኖር የተደረገበት ምክንያት በተለይ በሃገራችን የሚበዛው ገበሬ ድሃ ስለሆነ ትንሽ ሲቸግረው መሬቱን ይሸጣል፤ በዚህም መሬት በጥቂት ሰዎች እጅ በመከማቸት ጥለነው የመጣነውን የፊውዳሉን ስርዓት ይመልስብናል ይላሉ። ስለዚህም ገበሬውን ለመጠበቅና ሄዶ ሄዶ ሊፈጠር የሚችለውን የመሬት ከበርቴ ስርዓት ለመከላከል መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ሃብት መሆን አለበት ብለው ያምናሉ። መሬት ይሸጥ ይለወጥ ተብሎ ቢፈቀድ አርሶ አደሩ መሬቱን ሸጦ ከተማ ይገባል የሚለው የስጋት ሀሳብ ግን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ምክንያቱም ግብርና እንደ ሌሎች የስራ መስኮች ሁሉ ጥረትና ክህሎት የሚጠይቅ ስለሆነ በዚህ ዘርፍ ያልተሳካለት ሰው መሬቱን ሸጦ ወደ ከተማ ሲገባ አዋጭ ተብለው በተጠኑ የስራ መስኮች እንዲሰማራ ወይም አማራጭ ስራ እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ እንጂ መሬት ባለቤትነቱን መንፈግ አሳማኝነት የለውም። መሰረተ ልማት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች መሬት የግለሰቦች ቢሆን መሰረተ ልማቶችን ለማስፋፋት ግለሰቦች ከፍተኛ ገንዘብ ሊጠይቁ ይችላሉ የሚለውም መከራከሪያቸው ቢሆን ያን ያክል የሚስኬድ አይደልም። ምክንያቱም እኝህን መሰል ስጋቶችን አስገዳጅ የህግ ማዕቀፎችን በማርቀቅና ከመሬት ፖሊሲው ጋር በማካተት በቀላሉ መፍታት የሚቻልበት መንገድ ስላለ። መሬት እንዲሸጥ ቢፈቀድ የፊውዳሉ ስርዓት ይመለሳል የሚለው መከራከሪያም ቢሆን ውሀ የሚቋጥር አይደለም። ምክንያቱም አንዳንድ ገበሬዎች ብዙ መሬት እየገዙ የመሬት ሃብታም ስለሚሆኑና ያ የሸጠው ገበሬ የነዚህ የመሬት ሃብታሞች የቀን ሰራተኛ ስለሆነ የፊውዳል ስራዐት ይመለሳል ማለት አይደለም። ከሁሉ በላይ ግን ሃብታም እየሆኑ የሚመጡ ገበሬዎች ሌሎች መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ሃብት ያላቸውን ገበሬዎች በእርሻ መሬቶቻቸው ላይ ማሰራት መጀመራቸው የካፒታሊስት ስርዓት መገለጫ ነው። ፍትህ እስካለ ድረስ የካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ የሚኖር የሃብት መበላለጥ ሀገርን ሊጎዳ አይችልም። በፊውዳሉ ስርዓት ውስጥ ጭሰኛው ምንም አይነት የህግ ከለላ የለውም። ፊውዳሉ ከህግ በላይ ነው። አሁን ግን የመሬት ከበርቴ ቢፈጠር ይህ ከበርቴ ከህግ በላይ እንዳይሆን መንግስት አለ። የሚቀጥራቸውን ሰራተኞች ተገቢ የጉልበት ዋጋ እንዲከፍልና መብታቸውን እንዲያከብርላቸው ይገደዳል:: በመሆኑም የመሬት ሃብታም ማፍራት ወደ ፊውዳል ስርዓት ኢትዮጵያን አይመልስም። ከፍ ሲል እንዳልኩት የህግ የበላይነት ስለሚኖርና መንግስትም ህግን የማስከበር ሃላፊነት ስላለበት ይህ አይፈጠርም። ዋናው መንግስት መጠንቀቅ ያለበት የጉልበት ዋጋን ፍትሃዊነት ማጤንና ሰባዊ መብትን ማስከበር ላይ ነው። ይህ ከሆነ የመሬት ሃብታም ማፍራት ወደ ፊውዳል ስርዓት ኢትዮጵያን አይመልስም።

ሁለተኛው ችግር በርካታ ህዝባችን ህይወቱን በግብርና ዘርፍ እንዲመራ መገደቡ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ 80 በመቶ ሕዝብ የሚኖረው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ በከተሞች የሚኖረው የሕዝብ ብዛት 20 በመቶ ብቻ ነው። ገጠር የሚኖሩት 80 በመቶ ገበሬዎች፣ 20 በመቶ የሆነውን የከተማ ሕዝብ መቀለብ አልቻሉም:: በአሜሪካ ግን ገበሬው 2 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ብቻ ነው። ሌላው ህዝብ ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ ዘርፎች የተሰማራ ነው። እነዚህ ሁለት በመቶ የሚሆኑ ገበሬዎች የተቀረውን 98 በመቶ ሕዝብ አብልተው፣ አጥግበውና ለዕርዳታና ለውጭ ገብያ የሚሆን የምግብ ምርት ጭምር ያመርታሉ:: በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ያደጉ ሀገሮች የመላ ሀገራቸውን ህዝብ የምግብ ዋስትና አረጋግጠው ለውጭ ገብያም የሚያቀርቡትን ምርት የሚያመርተው ገበሬ ቁጥር እጅግ በጣም ትንሽ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው የገበሬው የመሬት ይዞታ ከኛ ሀገር በተቃራኒ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ ነው። እኚህ ጥቂት አርሶ አደሮች እጅግ ሰፋፊ መሬት ባለቤቶች ናቸው። እኛ ሀገር ገበሬዎች እጅግ በርካታ ሁነው የመሬት ይዞታቸው ግን በአማካይ በጣም ጥቂትና የተበጣጠሰ ነው። ገበሬዎች በጣም ሰፊ መሬት ሲይዙ ከፍተኛ ምርት ማምረት ይችላሉ። ይህም Economy of Scale እንዲፈጠር ወይም በርካታ ምርት በማምረት ለእያንዳንዱ ምርት የግብዓት ወጭን እንዲቀንስ ይረዳል። በአብዮቱ ማግስት የደርግ መንግስት በወሰደው የመሬት አየያዝ ማሻሻያ (መሬት ላራሹ)፤ መሬት በእጅጉ እንዲበጣጠስ በር ከፍቷል። ከዛ ቀጥሎ የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መምጣትም የመሬት መበጣጠሱን አባብሷል። የሀገራችን የመሬት ፖሊሲም ቢሆን የመሬት መሸጥና መለወጥን የሚያበረታታ ባለመሆኑ ምክንያት ለበርካታ ገበሬዎች የተበጣጠሰው መሬት ወደ ጥቂት ዉጤታማ አርሶ አደሮች እንዳይሰበሰብ በር ዘግቷል። በዚህም በግብርናው ዘርፍ Economy of Scale እንዳይፈጠር በማድረግ የግብርናውን ዘርፍ በእጅጉ እየጎዳ ይገኛል።

ሶስተኛው መከራከሪያዬ የህዝብ ቁጥር እየበዛ መምጣትን ተከትሎ የተከሰተው የተበጣጠሰ መሬት አየያዝ ችግር እንዳይፈታ ይገድባል የሚል ነው። ይኸውም የተበጣጠሰ የመሬት አየያዝ ገበሬው ከድህነት አዙሪት (Viscous Circle

of Poverty) እንዳይወጣና ግብርናውን በተለያዩ ግብዓቶችና ቴክኖሎጅዎች በመደገፍ ምርትን መጨመር እንዲሁም ከአመት ሁለትና ሶስት ዙር የማምረት እንቅስቃሴን እንዳይሞክረው ብቻ ሳይሆን እንዳያስበው የሚያደርግ ነው። ገበሬው በራሱ አቅም የግብርና ግብዓቶችንና የቴክኖሎጅ ውጤቶችን መሸመት፤ የግብርና ባለሞያዎችንም ቀጥሮ ማሰራት የሚችለው የሰፋፊ መሬት ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው። ከአንድና ሁለት ሄክታር የማይበልጥ ቁራሽ መሬት ይዞ ግን ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች ሊያስብ አይችልም። ቢይስብም ሊተገብራቸው አቅም አይኖረውም። መጀመርያ ባለችው ጥቂት ወረት መሬቱን እንዲያሰፋና ምርቱን እንዲጨምር ሊፈቀድለት ይገባል። ከዚያ በኋላ ይህንን ወረት እያሰፋ ጎን ለጎንም ቴክኖሎጅን እየለመደና ለስራው እያዋለ ወደ መካናይዜሽን የሸጋገራል። ለምሳሌ ሁለት ሄክታር መሬት ያለው ሰው የውሀ ጉድጓድ ቆፍሮ የመኸር ግብርና ለማከናውን ፍላጎት አይኖረውም። በግሉ የግብርና ባለሞያ ቀጥሮ ግብርናውን ባሳይንስ ለመደገፍ አያስብም። ትናንሽ የግብርና ስራ መከወኛ ማሽነሪዎችን የመግዛት አቅም አይኖረውም። ቢኖረውም እንኳን ካለው ውስን የመሬት መጠንና ለእኚህ ጉዳዮች ካወጣባቸው ወጭዎች አንፃር ብዙ ጥቅም የሚያስገኙ አይሆኑም። ሰፊ መሬት ያለው አርሶ አደር ግን ከላይ የዘረዘርናቸውን ነገሮች ለማድረግ አይቸገርም። እኚህን ነገሮች ቢተገብር ካወጣባቸው ወጭዎች በላይ የሚያገኘው ጥቅም ከፍ ያለ ነው።

አራተኛው በጣም ጉልህ ችግር ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ችግሮቹ ናቸው። መግዛትና መሸጥ የኢኮኖሚ አስኳል ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ከሌሉ ገበያ የለም ማለት ነው። ገበያ ከሌለ ደግሞ እድገትንና ፈጠራን ማሰብ አይቻልም። በገበሬው መካከል መሸጥና መለወጥ አይኖርም ማለት ገበያን ከገበሬው ህይወት ማውጣት ነው። በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ፍላጎትና አቅርቦትን የሚገድብ ህግ ማውጣት ኢኮኖሚ እያዳይንቀሳቀስ ሰንክሎ መያዝ ማለት አይደለምን? የኢትዮጵያ መሬት ከመግዛትና ከመሸጥ መብት ሲከለከል በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ በእርሻ ላይ በጣም ጥገኛ በሆነ አገር ላይ ከፍተኛ የሆነ የማክሮ ኢኮኖሚ ተጽእኖ ያመጣል። ከዚ በተጨመሪም መሬት በሕገ መንግሥቱ ‹‹የሕዝብና የመንግሥት›› ነው ቢባልም፣ ካድሬና ደላላ መሬትን በመቀራመት እየከበሩበት እንደሆነ በተደጋጋሚ ይነሳል። መሬት ለታለመለት ዓላማ አለመዋሉን፣ እንዲያውም የሙስናና ምዝበራ ምንጭ መሆኑም በስፋት ይነገራል። በተንጠለጠለና የባለቤትነት ዋስትና በማይሰጥ የመሬት አሠራር ሕግ የዘለቀው ግብርና ከፋይናንስ በተጓዳኝ ቴክኖሎጂና ዕውቀትን የሚስብ አዋጭ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲሆን ከተፈለገ የመሬት ባለቤትነት መብትን ማሻሻል ለነገ የማይባል ተግባር ነው።

በአጠቃላይ የመሬት ፖሊሲያችን ለገበሬው መሬቱን የመሸጥና የመለወጥ መብት ቢጎናፀፍ የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ይጨምራል፤ ለኢንዱስትሪ ሴክተሩም ግብዐት ይሆናል። ይህ ደግሞ ጠቅላላ የኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል። ገበሬ የመሬቱ ሙሉ የባለቤትነት መብት እስከ መሸጥ መለወጥ ሊረጋገጥ ይገባል። ስለዚህ ይህ የመሬት ባለቤትነት መብትን የያዙ ፖሊሲዎች እንዲሻሻሉ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። ሙህራኑ በጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ጥናትና ምርምር ማድረግ አለባቸው። ፖሊሲ አውጭዎችም ጉዳዩን ዳግም ሊፈትሹት ይገባል። ወጣቱም ከአላፊና ስሜት ኮርኳሪ ጉዳዮች ይልቅ እንደዚህ አይነት በቀጥታ ህይወቱ ላይ ተፅዕኖ ያላቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን ማድረግ ይገባዋል። የኔ ትውልድ ከ1960ቹ ትውልድ መማር ያለበት ከጊዜያዊና ረብ የለሽ ጭቅጭቆችና መገፋፋቶች በመውጣት ይህንና ይህን መሰል ዘላቂና ዘመን ተሻጋሪ ጥቅም የሚሰጡ ሀሳቦች ዙሪያ መወያየትን ልምድ ማድረገን ሲሆን ይገባል። እልፍ ሲልም ዘመኑን የሚዋጅና የወጣቱን ፍላጎት መዐከል ያደረገ የፖሊሲ ማሻሻያ እንዲመጣ በንቃት መታገል አስፈላጊ ነው። ይህን ማድረግ ካልቻልን ግን ባረጁና ባፈጁ፤ ዘመናችን በማይመጥኑን ህጎችና ፖሊሲዎች እጣ ፋንታችንን አሳልፈን ለመስጠት እንገደዳለን። ይህ ደግሞ በዚህ የቴክኖሎጅ፣ ኢንፎርሜሽንና ዲጅታላይዜሽን ዘመን ተወዳድሪ መሆን እንዳንችል እንቅፋት የሚሆንና የበለጠ ወደ ኋላ እንድንቀር የሚያደርግ ነውና ሊታሰብበት ይገባል።

## ይድነቃቸው ሰለሞን: ኢትዮጵያን ማሰብ፡ ከብሄር ፖለቲካ ለማምለጥ የቀረበ ሥግራዊ የመፍትሄ ሃሳብ

### ደወል 1: የልጅነቴ እንቆቅልሽ በሰላሌ

ሀገሬ ውብ ናት። በባህር ዛፍ፣ በጽድ፣ በሸውሸዌ፣ በግራዋ፣ በኮባ፣ በደማከሴ፣ በኮሰረት፣ በጤና አዳም፣ በአክርማ፣ በሰርዶ፣ በጠጅ ሳር፣ በህበረቀለማም አበቦች እና እነዚህ በሚጠሯቸው አዕዋፍትና በንቦች እና በልጆች ጨዋታ የደመቀች ናት፣ ግቢያችን። ይህን ድምቀት ለመፍጠር ገንዘብና ጉልበት ወጥቷል፤ ለደቅዳቂ፣ ለቆፋሪ፣ ለችግኝ፣ ለችግኝ ተካይ፣ ለኮትኳች እና ማታ ማታ እናቴ ለምታጠጣው ውሃ ጭምር። ጠዋት ጠዋት የእናቴ ቁርስ እስኪደርስ የግቢያችንን ትንፋሽ እየማግኹ ስንሸራሸር የተለየ ስሜት ይሰማኛል። ከመንደራችን በስፋት፣ በዛፍ፣ በአበቦች አይነትና ብዛት ግቢያችንን የሚበልጠው አብዲሳ አጋ ትምህርት ቤት ብቻ ይመስለኛል። ትምህርት ቤቱ ቅርብ እና እናቴም የምትሰራበት በመሆኑ እንደግቢያችን ነበር። መስከረም 1986 ዓ.ም. አብዲሳ አጋ ትምህርት ቤት የአማርኛ ተማሪ አልቀበል አለ። በዚህ ምክንያት በ6 ዓመቴ ከመኖሪያ ቤቴ አንድ ሰዐት በራቀው አብዮት ፍሬ ትምህርት ቤት ሄጄ አንደኛ ክፍል ተመዘገብኩ። በርቀቱ አባቴ ዘውትር ይበሳጫል፤ ጺሙን እየላጨ፣ ከረቫቱን እያበጀ፣ ሽቶ እየነሰነሰ፣ መሃረብ እያጠፈ፣ ጫማውን እያሰረ፣ ጸጉሩን እያበጠረ፣ እየተመገበ ... ሁሉ በዚህ ጉዳይ አብዝቶ ይበሰጫል።

- --አማርኛን በመዝጋት ኦሮሞን መጥቀማቸው ነው!?
- --የራስህ ጓደኛ ነው በቂ የአማርኛ ተማሪ የለም ብሎ ሪፖርት ያቀረበው
- --እኔ የቋንቋ በሽታ የለብኝም
- --በርታ በርታ አይዞህ -- የደብተር ቦርሳዬን ሸክፌ ስወጣ

የበራችንን መቀርቀሪያ ከመሸጎሪያው ነቅዬ እየተከልኩ ጤዛ በሸፈነው በፊትአውራሪ አምዴ አበራ ሜዳ አሳብሬ ወደ አብዮት ፍሬ ትምህርት ቤት ሳዘግም አቶ ካቻ «ብርዱ ብርድ ነው የአህያ ቀንድ ነው» እያለ እንደስሙ በሶምሶማ አልፎኛል። አባባ በተደጋጋሚ «የቋንቋ በሽታ የለብኝም» ሲል አድምጨዋለሁ። ምን ማለቱ እንደሆነ አልረዳውም።

ከአብዲሳ አጋ ወደ አብዮት ፍሬ ያደረግሁት ጉዞ የቋንቋ ፖለቲካ የፈጠረው መፈናቀልና አጥንት ሰባሪ ስደት እንደሆነ እጅግ ዘግይቶ ምክንያቱ ገብቶኛል። ዛሬ ዛሬ ተረድቻለሁ። በቋንቋ የተመራ ፖለቲካ አሳዳጅ እና አፈናቃይ እንደሆነ ተገንዝቢያለሁ። ሃገሬን፣ የቋንቋ ፖለቲካ የፈጠረው ቀውስ በሃገር ውስጥ ስደት ከዓለም ቀዳሚዋ አድርጓታል። እኔ በምኖርበት የደብረ ብርሃን ከተማ ብቻ ወደ 90,000 የሚጠጋ ተፈናቃይ ይማቅቃል። መፈናቀሉ ከሥፍራ ብቻ ሳይሆን ከህሊና ጭምር በመሆኑ በስነልቦናም ታጉለዋል። ማህበራዊነት ከስሩ ተደምስሶ ሰላማቸውን ተነጥቀዋል። የድርሰቴን መንፈስ እንዳይረብሽ ስለምስጋ እና ለቀባሪው ማርዳት ስለሚሆን በፖለቲካው ምክንያት የደረሰውን የህዝብ መፈናቀል፣ ሞት እና ውድመት ማስረጃ ከመጥቀስ እቆጠባለሁ። ይሄ ሁሉ መካራ ለምን ደረሰብን?

የዚህ ድርሰት ዓላማ በኢትዮጵያ «የብሔር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች» ፖለቲካ (ከዚህ በኋላ የብሄር ፖለቲካ) እንደሀገር ካስከተለብን ችግር ለመላቀቅ ብሄርን ማስገር በሚል ዘይቤ መፍትሄ ተኮር ሃሳብ ማቅረብ ነው። ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ፣ ብሄር በጽንሰ ሃሳባዊ ብያኔው ‹ቋንቋ› እንደሆነ አስረዳለሁ። በመቀጠል፣ የላካንን ፍካሬ ልቦና መሰረት በማድረግ ቋንቋ እንዴት ፖለቲካውን አፈናቃይ ሊያደርገው እንደቻለ ሃተታ አቀርባለሁ። በመጨረሻም፣ ውሃ ያማያርሰው ንግግር የማያለሰልሰው ስለሴለ የኢትዮጵያ ፖለቲካን ውጥረት ለማርገብ ይረዳል በማለት የዴሉዝ እና ጓታሪን የማስገር ፍልስፍና እንደመፍትሄ እጠቁማለሁ።

## ደወል 2፡ አሰሳ ብሄር፡ የትርጉም አልቦነት ትክክለኛ ቀውስ

የዋለልኝ መኮንን «የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ» ድርሰት በኢትዮጵያ የብሔር ጭቆና መኖሩን በአደባባይ ከማወጁም ባሻገር የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጣ ፈንታ ላይ ጉልህ ድርሻ ተጫውቷል። በደርግ መንግስት መሻር ማግስት ተግባራዊ የተደረገው የኢፌዲሪ መንግስት የተቋቋመበት የማህበራዊ ውል ሰነድ ዓላማ የብሔር ጭቆና ውጤት የሆነውን ታሪካዊ የተዛባ ግንኙነት «ለማረምና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ» ነው። ነገር ግን፣ በተጨባጭ እንደታየው ህገ-መንግስቱ ከፖለቲካ አርዓያ አንፈግጦ ለማያባራ ማህበራዊ ቀውስ እና ለተራዘመ መከራ ዳርጎናል። እንደምኝ ዘፈን በሃገራችን የግጭት፣ የጭፍጨፋ፣ የመፈናቀል እና የስደት በአጠቃላይ የማህበራዊ ቀውስ ምንጭ የብሄር ተወላጅ መሆን አለመሆን ነው ሲባል ይደመጣል። ብሔር ምንድር ነው ብሎ ለመረመረ አሃዙ ፍች ግልጽ እንደሌለው ይገነዘባል፡ ፡ አንድ ጸሐፊ እንደገለጸው «ብሄር ራሱን በዘር፣ በባህል፣ በወንዝ እና በእምነት ተብትቦ በትልልቅ ተራሮች መካከል ተደብቋል።»(የኔ አጽእኖት ነው።) የሆነው ሆኖ፣ <u>በእኔ ሞጋች ድርሰት መሰረት እንደሀገር ለምንገኝበት የፖለቲካ ትርምስ ምንጩ በህገ-መንግስቱ የባለቤትነት መብት የተሰጠው እና አውራ ጽንሰሐሳባዊ የሆነው «ብሄር» የወከለው ዝክረነገር (መዝገብ) በግልጽ አለመደንገጉ የፈጠረው ትክክለኛ ማህበራዊ ቀውስ ነው።</u>

ከኢፌዲሪ ህገመንግስት እንደተገነዘብነው በኢትዮጵያ የብሄር ብያኔ በዋናነት ቋንቋን ማዕከል ያደረገ አስተዳደር በመሆኑ ፖለቲካውን በቋንቋ የተመሰረተ እና የተመራ እንዲሆን አድርጎታል። ለምሳሌ፣ ሩቀ ሳንሄድ በኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሄሮች ይገኛሉ ሲባል ከ80 በላይ ቋንቋዎች መኖራቸውን ከግምት አስገብተን ነው። በመሆኑም፣ የብሄርን ምንነት በተግባር ቋንቋ መር ነው። ስለዚህ፣ በኢትዮጵያ ያለው የብሄር ፖለቲካ ሳይሆን የቋንቋ ፖለቲካ ነው ማለት ይቻላል። ይህም በኢትዮጵያ የብሄር ጥያቄ ማለት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመተዳደር መብት ይከበር ጥያቄ ነው። ክርክሬን ለማጠንከር፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ መሰረታዊ ለውጥ ያስከተለውን የአብዮት ዘመን ከጉዳዬ አንጻር አመለክታለሁ።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር «ቋንቋና አብዮታዊ ትግል፤ ቋንቋዎች በኢትዮጵያ» በሚል በአዘጋጀው «ታጠቅ» መጽሔት አንድን ህዝብ በሚናገረው ቋንቋ ለመጥራት (ለመወከል) ሙከራ ነበር። በመጽሔቱ መግቢያ ላይም የሚከተለው ተመላክቷል። «የኢትዮጵያን የወደፊት ሪቮሉሽን ትልቅ ትርጉም ያለውና አስደናቂ ሊያደርጉ ከሚችሉት ነጥቦች አንዱ (የቋንቋ) ጉዳይ ነው። ‹የብሄሮች ቤተመዘክር› የሆነችውን ኢትዮጵያን ከፊውዳላዊ ጨለማ ከማውጣት የበለጠ የህይወት ምኞት ሊኖር እንደማይችል ያስገነዝባል። ... ቋንቋና ሪቮሉቲናዊ ትግል በጥብቅ የተሳሰሩ መሆናቸው ግልጽ ነው።» (1964፡6) ። ይህ የቋንቋ ጉዳይ በአብዮቱ ሂደት ቁልፍ አጀንዳ እንደነበር ይመሰክራል።

*የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት* በ1978 ዓ.ም. «አጭር የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ማወቂያ» በሚል የሳተመው

ጥራዝም በኢትዮጵያ የሚገኙ ቋንቋዎች መገኛ እና ስርጭት ካራታ ሆኖ ይገኛል፡፡ በ1987 ዓ.ም. የጸደቀው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት መሰረት በሃገራችን የብሄር («የብሄር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች») ማህበራዊ ውል ሰነድ የጸደቀው በኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ሥምምነት ነው ቢባልም የዚህ ጥቅል ብያኔ መሰረት ቋንቋ ነው፡፡

ከቋንቋ አንጻር በኢትዮጵያ የተለየ ሁኔታ እንዳለ ግልጽ ነው፤ አንድም ቋንቋ በብሄር ጭንብል ተደብቆ ይገኛል፤ ሌላም ቋንቋ የፖለቲከኞች የስልጣን ማግኛ መስፈርት ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ቋንቋ የማንነት መጠሪያም አድርገነዋል፡፡ ቋንቋ የመንግስት አስተዳደር ማዕከል ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ፣ የሲዳማ ክልል መሆንን ተከትሎ የተደረገው የመንግስት ሰራተኞች ሽግሽግ መስፈርት የሲዳምኛ ቋንቋ መቻል ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ተመሳሳይ መሆኑን ተጨባጭ መሳያዎች ብዙ ናቸው፡፡ በአጭሩ፣ በኢትዮጵያ የተፈጠረውን የፖለቲካ ውጥረት ለማርገብ የብሄር ፖለቲካን በቋንቋ ፖለቲካ ተክቶ መጥራትና መረዳት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ የሥነልሳን አስተማሪ እንደገለጹት ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀውስ ምንጩ ለቋንቋ ከሰጠነው ያልተጠና ፖለቲካዊ ብያኔ የመጣ ነው፡፡ እጠቅሳለሁ፡፡ «የኢትዮጵያ ቁልፍ ችግር ቋንቋ ነው፡፡ (ይህ) መሆኑ ገና አልታወቀም፡፡ በሐገራችን የማህበራዊ ሥነልሳን ሊቃውትም አልታወቀም ለማለት ይቻላል፡፡ የበለጠ ሊታወቅም የሚችለው ደግሞ፡ በማሕበራዊ ሥነልሳን ሊቃውንት እና በቋንቋ ምሁራን ነው፡፡ በተጨማሪም፣ በቋንቋ ምንነት እና መዋቅር ላይ በሚያተኩሩ ሊቃውንት ትብብር፡ ቋንቋ በሚገባ ተተንትኖ ሲታወቅ ነው፡፡ እንደኢትዮጵያ ላሉ ልሳነ ብዙ ሀገራት፡ ቋንቋ የህዝቡን ማህበራዊ ኑሮና፡ የስነ መንግስት ሂደት ሊያዛባ ይችላል፡፡» ነገር ግን፣ የቋንቋ ብዝሃነት በራሱ ችግር ሊሆን እንደማይችል ከሌሎች ልሳነ ብዙ አገራት እንገነዘባለን፡፡ በሃገራችን ታሪክም ቋንቋ መር ግጭት አልተዘገበም፡፡

የድርሰቴን ግብ ለማሳካት፣ ስለቋንቋ ምንነት በፈረንሳያዊው ፈላስፋ በጃኩስ ላካን መንገድ አቀርባለሁ፡፡ በአጭሩ፣ ላካን ሥነልሳንን መሰረት በማድረግ በፍሮይድ የተቀነቀነውን ፍካሬልቦናን ያዳበረ ፈላስፋ ነው፡፡ ተቀባይነትም አግኝቷል፡፡ የሥነልሳን አባት የሆነው ፈርዲናርድ ዲ ሳሱ እንዳበሰረው በቁስ እና በስያሜ (ምልክት) መካካል ምንም አይነት ቀጥተኛ ግንኙነት የለም፡፡ ይህ ግንኙነት ዘፈቀዳዊ (arbitrary) ነው፡፡ በስነ-ልሳን በሁለት አውታሮች (the signifier and the signified) መካከል የሚገኘው ክፍተት የማይደፈን ነው፡፡ ላካን ይህን ግኝት ወደ አዕምሮ ጥናት አምጥቶ ባደረገው ጥናት የኢ-ንቁ (ፍዙ) አዕምሮ ክፍል ግንባታው እንደቋንቋ መሆኑን እንደሚከተለው አስረድቷል፡፡

በግለሰብ-ማህበረሰብ ቁርኝት የሚገነባው ማንነት ያለቋንቋ አይታሰበም፡፡ ምክንያቱም በቅድመ-ቋንቋ (በአራስነት) ራስን መለየት አይቻልም፤ ይልቁን ህጻኑ ፍጹም እርሱነቱንና አከባቢውን ማገናዘብ ባልቻለበትና ራሱን በእናቱ የመሰለባቸውን (Imagery) ደረጃዎች አልፏል፡፡ ቋንቋ በስዕላዊ ደረጃ ካዳበርነው ግንዛቤ በተቃራኒ የተለየ ንጥል ማንነት ይሠጠናል፡፡ ከዚህ በኋላም ህፃኑ እናገኘዋለን፡፡ ሰው በቋንቋ ባህሉንና የማህበረሰቡን የግንባታ ምሰሶዎች እየተረዳ ያድጋል፡፡ በእነዚህ እውቀቶቹም እየተመራ ፍላጎቶቹን ይጨፈልቃል፡፡ ይህም ቋንቋን የስሜት መጨቆን መንስኤ እና ውጤት ያደርገዋል፡፡

በላካን ፍካሬ ልቦና መሰረት ሰው የሚተዳደረው ቋንቋን መጠቀም በጀመረበት ቅጽበት ጀምሮ በሚገነባው የኢ-ንቁ የአዕምሮ ክፍል ነው፡፡ ቋንቋ መቻል ትዕምርታዊ (Symbolic) ወደ ሆነው ባህል መር ስርዐተ ማህበር ያሸጋግረናል፡፡ በግልፅ አቀራረብ፣ ቋንቋ የሰው ልጅ ማንነት የሚፈጠርበት፣ የሚታነጽበትና የሚበለጽግበት ቢሆንም ቅሉ ቋንቋ አሰራሩ በተለዋጭ እና በስምአዳሪ ዘይቤ አማካኝነት፡ አንድም ራሱን በመለወጥ አንድም በሌላ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ በመሆኑ ቋንቋ ቋሚ የረጋና የጸና ጽንሰሃሳብ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ ቋንቋን ኢ-አምክኖአዊ ያደርገዋል፡፡

ከላካን ፍካሬልቦናዊ የቋንቋ ሃተታ እንደምንማረው አንድን ጉዳይ ለመግለጽ የምናደርገው ሙከራ በአደገኛ ሁኔታ ጉዳዩን ከመረዳት እንታቀባለን፡፡ ለአንድ እሳቤ የሚሰጥ ስያሜና ማብራሪያ ጉዳዩን በትክክል እንደሚያሳይ ሁሉ ደብቆታል፡ ፡ ለምሳሌ፣ ከላይ እንደጠቀስኩት ለብሄር የተሰጠው ሥያሜ የቋንቋን ምንነት ደብቆታል፤ የፖለቲካ ማብራሪያውንም በእጅጉ አዛብቷል፡፡ ይህም ማለት በቋንቋ እየተመራ ይሆነኝ ብሎ እውነታን ለመገልበጥ የሚደረግ የተሳሳተ አሰያየም በተፈጥሮ አዕምሮ ዘንድ ቅቡልነት የማግኘት ብርቱ ተግዳሮት ይገጥመዋል፡፡ ይህ ምትክ ትርጓሜ ማጣት በላካን እሳቤ ትክክለኛ ቀውስ (trauma of the real) ይባላል፡፡ ህመም ፈጣሪም ነው፡፡

በተጨማሪም፣ በቋንቋ ለመተዳደር መሞከር እንደአሰላሳይ ሰው ሳይሆን እንደቁስ በራሳችን ላይ የማንቆጣጠረው ተቆጣጣሪ እንደማንገስ ነው፡፡ በዚህ ረገድ እንደ ሐቢብ ያሉ አጥኝዎችን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በእኔ ግንዛቤ ኢትዮጵያ የመፈናቀል ትርምስ፣ የፍርሃት መናሃሪያ እና የጭቆና ማዕከል የሆነችበት ምክንያት ፖለቲካው የተቀዳው ከመዋቅረ ቋንቋ በመሆኑ ነው፡፡ በማንነት ከፋፍሎ እንዲያባላን ለቋንቋ ህጋዊ ሥልጣን ሰጥተነዋል፡፡ ለሰው አይደለም መብት የሰጠነው፡፡ ምክንያቱም፣ ሰው በቋንቋ እየተመራ ይሄዳል እንጂ ሰው ቋንቋን እየመራ መሄድ ስለማይችል ነው፡፡ በአገራችን የተከሰተው መፈናቀል እና ስድት ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ይሆናል፡፡ እኔ እስከማውቀው በአጠቃለይ የኢትዮጵያ ታሪካ እና ባህል ውስጥ ይህን መሰል ጉዳይ አልተስተዋለም፡፡ አሁን ከየት መጣ? ከቋንቋ መር ፖለቲካ ተጸንሶ ስለተወለደ ነው፡፡

በጥቅሉ፣ ከቀረበው ሃተታ ውስጥ የሚከተሉትን በልብ ማድረግ የተገባ ነው፡ ቋንቋ የጭቆና መንስኤ-ውጤት መሆኑ፣ ቋንቋ ክዋኔው ማፈናቀል እና መውረስ መሆኑ፣ ቋንቋ የሚዋዥቅ ጽንሰ ሃሳብ መሆኑ፣ ቋንቋ ኢ-ምክንያታዊ መሆኑ እና ምትክ ትርጉም ማጣት ህመም ፈጣሪ መሆኑ ናቸው። የሀገራችን ፖለቲካ በቋንቋ የተመራ ነው። ይህ ክስተት የቋንቋ ስፍራ በፖለቲካው ስፍራ እንዲገባ አድርጎታል። ይህ የተለያዩ heterogeneous መስኮች መቀላቀል መግቢያ እና መውጫ የሌለው ውስብስብ ሁኔታን ይፈጥራል። በዚህ ግዜ ስግር ይፈጠራል። ይህ ሃሳብ ኢትዮጵያ ለምትገኝበት ዘርፈብዙ ምስቅልቅል ተጨባጭ ማስረጃ ከመሆኑም ባሻገር ቋንቋን መሰረት ያደረገው የብሄር ፌደራሊዝም ቋሚና የረጋ ህብረተሰብ እንዲሁም የጸና አገር የማቆምና የማስቀጠል እድሉን ጥያቄ ምልክት ውስጥ ከቶታል።

## ደወል 3፡ *ሥግራዊነት፡ አማራጭ መፍትሄ*

ጊለስ ድሉዝ እና ፍሌክስ ጓታሪ የተባሉ የፈረንሳይ ፈላስፎች እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1976 ወይም በ1984 አም በጻፉት ሺህ አንባዎች በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ Rhizome (ሥግር[1]) የተሰኘ ጽንሰሃሳብ አፍልቀዋል። ይህ ጽንሰሐሳብ በአጭሩ የምንገኝበትን ዘመን ውስብስብነት አመላካች ነው። ስግር (ራይዞም) ከእጽዋት ሳይንስ የተቀዳ ከተክል የሥር እንቅስቃሴ ጋር የሚናበብ ልዋጭ ዘይቤ ነው። የስግር ተቃራኒው ዛፍ ነው። በሃገራችን ዛፋዊነትን የሚያገልጽ ግጥም ከበዕውቀቱ ስዩም እንመለከት።

### *‹‹መሆን ከተመኘህ ዛፍነትን ምረጥ፤*
### *ቆርጠውኽ ሲሄዱ ሺህ ሆነህ አቆጥቁጥ።››*

ስግራዊነትን ለሚያቀነቅኑት የግጥሙ ጭብጥ ያረፈበት ዛፋዊ እሳቤ ዘመኑን ያልዋጀ (aborescent thinking) ነው፡፡ አይዋጅም። ማለትም፣ የቁጥር ብልጫ ነጻነትን አያጎናጽፈንም። በዚህ ዘመን ነጻነትን ለማግኘት የሃሳብ ጥራት፣ ለብዝሃነት፣ ተለዋዋጭነት (flexibility) ፣ ለአካታችነት እና ለሌሎችም ወዘተ ብልሃቶች ዝግጁ (ክፍት) መሆን ያስፈልጋል። በጉልህ ከምንመለከተው አውድ ተላቀን *የሥር እንቅስቃሴን* ባህሪይና ዘይቤ በመውረስ ለማሰብ መነሳሳት *ሥግራዊነት* ነው።

*የሥር ንቅናቄው* ከታች በመገኘቱ ከበላይ የሚመጣን ጫናን (ጭቆናን) ይቋቋማል። በዚህ እንቅስቃሴ መሃል እና ዳርቻ የለም፤ መጀመሪያ መጨረሻ የለም፣ ሃሳብም የተከበረ እና የተገለለ አማባገነን ቦታ አይዝም። በመሆኑም ስግር የማያቋርጥ ውይይት ለሆነው ፖለቲካ መሰረታዊ ጉዳዩ ነው። ስግራዊነት የመሆን እድል (of becoming) ከመፍጠሩም ባሻገር አዳም ረታ እንደገለጸው ‹‹የአሁን ግዜ ቀጠና ውስጥ የመግባት እድል አለው።››

በዚህ ድርሰት እንደተገለጸው በቋንቋ የተመራው የሃገራችን ፖለቲካዊ ቀውስ በላሉ ሊፈታ የማይችልና ውስብስብ ነው። ስለዚህ ከቋንቋ መር የፖለቲካ እሳቤ ማምለጫ መስመር ሊፈለግለት ይገባል። ይህን ለማድረግ በስግራዊነት ግንዛቤ ተመርተን አማራጭ መፍትሄ መፈለግ የተገባ ነው። ይህን ማለት ጉዳዩን መተው ወይም ጉዳዩን መቀየር ማለት አይደለም። ይህን ማለት ጉዳዩ የጋራ አጀንዳ እንዲሆን ቤተሰብን ጨምሮ ከቀበሌ እስከ ከፍተኛ የመንግስት እርከን የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን ትብብር መፈለግ ነው። ምክንያቱም በስግራዊነት ስናስብ የምናስበው ስለብዙ ነገር ነው፤ በቁጥጥራችን ሥር ስለሚገኙ ነገሮች እና ከቁጥጥራችን ውጭ ሊገኙ ስለሚችሉ ነገሮች ጭምር። በስግራዊነት ስናስብ የምናስበው ስለመጀመር እና ስለመጨረስ አይደለም፤ ከምንገኝበት መሃል ተነስተን በዚህ መሃል በማለፍ ወደ መገናኘት እና መጓዝ ነው። በዚህ ማካከል አገራችን ከመቻቻል ፖለቲካ ወደ መተሳሳብ ፖለቲካ ልትገባ የምትችልበትን የበረራ መስመር (line of flight) ልናገኝ እንችላለን። ይህ አብዮታዊ ደወል የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሞገድ ነው።

እንደሃሳቡ አምጭዎች የፍሮይድ እና የላካን የሰው ልጅ ከቤተሰቡ (ከባህል) ጀምሮ ከሚያጋጥመው የመታመቅ ወይም የጭቆና ልምድ የተነሳ ይታወካል ከሚለው በዛፋዊነት ተጫኝና ጨፍላቂ የፍካሬልቦና (የሎጂክ፣ የስነልሳን፣ የዘረመል ወዘተ መስኮች መገለጫም ይሆናል) እሳቤ መላቀቅ አለብን። የማስገር ዓላማ እንደቋንቋ በቀላሉ ሊመዘኑ፣ ሊለኩና ሊመትሩ የሚችሉ ጉዳዮችን በመተው ሰዎችን ከሚገኙበት ችግር በኩል ለማግኘት (ለመያዝ) መሞከር ነው። ይህም ከሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ (ችግር) መውጫ እንዲያበጁ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል። ለምሳሌ በደወል አንድ እንደተገለጸው በ1986 ዓ.ም. አብዲሳ አጋ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማሩን አቁሞ ነበር፡፡ ስለሆነም፣ ይህ ፖለቲካዊ ውሳኔ ማህበረሰቡን ለከፍተኛ እንግልት የዳረገ በመሆኑ ለአስተዳደሩ በተደጋጋሚ ቅሬታ ይቀርብ ነበር። ከሶስት አመት እንግልት በኋላ በ1989 ዓ.ም. ውሳኔው ተሸሮ አብዲሳ አጋ የአማርኛም የኦሮምኛም ትምህርት ቤት እንዲሆን ተደርጓል። ክስተቱ ከአግላይነት አካታችንት ለማህበረሰብ ሰላም ወሳኝ እንደሆነ ትምህርት ሰጭ ሆኗል። የዳበረ አካታችነት የስግራዊነት አንዱ መገለጫ ነው።

---

1 ስግር Rhizome የተባለ ቃል የያዘውን ፍሬ ነገር ተክቶ ልንጠቀምበት እንደምንችል ደራሲ አዳም ረታ አስረድቷል። ዩምቤርቶ ኤኮን ጠቅሶ አዳም ረታ እንዳስቀመጠው ‹‹ ራይዞም አንዱመስመር ለኬሎች መስመሮች ጋር የተያያዘ ነው። ማዕከልም ደርዝም የለውም፡፡ መውጫም የለውም። የግምት አለም የራይዞም አለም ነው።››

## CREDITS

The Ethiopia Peace Research Facility (PRF) is an independent facility combining timely analysis on peace and conflict from Ethiopian experts with support for conflict sensitive programming in the country. It is managed by the Rift Valley Institute and funded by the UK government. The Rift Valley Institute works in Eastern and Central Africa to bring local knowledge to bear on social, political and economic development.

The Institute for Peace and Security Studies (IPSS), established in 2007 at Addis Ababa University (AAU), is a leading African institute for the production and dissemination of knowledge on peace and security, and is recognised for academic and research excellence. Over the years, the Institute has continued to achieve its vision through its state-of-the-art academic programmes and evidence-based research. It is also the secretariat of the Tana High-Level Forum on Security in Africa, an annual high-level gathering of African heads of state, former heads of state, eminent African personalities and experts to deliberate on the continent's most pressing peace and security issues. The IPSS also serves as the African Research Universities Alliance (ARUA) Centre of Excellence on Post-Conflict Societies.

Copyright © Institute for Peace and Security Studies and Rift Valley Institute 2024. This work is published under a Creative Commons AttributionNonCommercial-NoDerivatives License (CC BY-NC-ND 4.0)

IPSS Institute for Peace and Security Studies

Rift Valley Institute MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility